ጥላ ነሐሴ 2005 ዓ.ም 2ኛ ዓመት ቁ 7     TILA August 2013 2nd Year 7th Edition

# አባይ ሊያለማን ወይስ ሊያጠፋን?





በሞቃዲሹ የተከሰከሰው የኢትዮጵያ አውሮፕላን


የአግአዚው ቫንዳም -ኮፈሌ




**Freedom of expression is one of our most precious rights. It underpins every other freedom and provides a foundation for human dignity. Free, pluralistic and independent media is essential for its exercise."**

*UN Secretary-General Ban Ki-moon*
*and UNESCO Director-General Irina Bokova*

# ጥላ


## ዋና ስራ አስኪያጅ — General Manager
**መስፍን አብርሃ — Mesfin Abraha**

## ዋና አዘጋጆች — Editor In Chiefs
**እየሩሳሌም ሱሞሮ — Eyerusalem Sumoro**
**ዳዊት ፋንታ — Dawit Fanta**

## አዘጋጆች — Editors
**ዮሃንስ ሳምሶን — Yohanes Samson**
**ደበበ ከበደ — Debebe Kebede**
**ፍስሃፅዮን ሃይለገብርኤል — Fisshatsion Hailegeberile**

## ጽሁፍ አስተባባሪዎች — Coordinators
**ብርሃኑ ባዩ — Berhanu Baue**
**ኤደን ዳዊት — Eden Dawit**
**አስናቀች ጥላሁን — Asnakch Telahun**
**ህይወት ጥላሁን — Hiwot Tilahun**
**ወልደኪሮስ አስፋው — Weldekiros Asfaw**
**ዮርዳኖስ ሃ/ጊዮርጊስ — Yordanos Hailegiorgis**

## የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር — Computer Graphics
**ህሊና ዳዊት — Hilina Dawit**
**ዘውድነሽ ንጋቱ — Zewdinesh Nigatu**



**የጥላ መጽሔት አድራሻ/Tila Magazine Address**
**Mesfin Abraha**
**An der Obergeis 1**
**36251 Bad Hersfeld**
**Email:- tilamagazine@yahoo.de**
**Web-Site:- tilamagazine.yolasite.com**
**Tel.No.:- 015222195567,**
**017668830082, 017671668780**

# ማውጫ


አባይ ሊያለማን ወይስ ....... 7

ጨቋኙን ስርዓት በቃህ ልንለው......... 10
ስቃይና እንግልት ... 10
ሰላም 10

የወያኔ በደሎችና.... 10
የወቅቱ ህዝባዊ ንቅናቄ 11

ወያኔና አምስቱ መዘዞቹ 11

ወያኔና... 11

ሙሰኝነትን መዋጋት... 12
ቀን የጎደለብን... 12

የሙስሊሙ ስቃይ ... 12

ካርቱን 13
አመፅ አልባ አብዮት... 14
በአንድነት የመታገያው... 14

የሴቶች መብት ረገጣ 14
የትግሉ አስፈላጊነት 14
የድርሻችንን እንወጣ 14
የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት 15

በቃ 15
ለለውጥ እንታገል 15
አባይን ለፖለቲካ መሳሪያነት... 16
መፍትሔው እኛው ነን 16
ኮፈሌ በደም ታጠበች 17
ኢትዮጵያን እናድን 17

Eid Mubarek 18
Water politics in Nile ... 19

Amhara`s suffered... 19

Egypts situation... 19
Justice for Oromo… 20

No Human right... 20
TPLF Atrocities … 21

We Must Struggle… 22
Wir wünschen… 22

We are … 22


**መልካም ንባብ**
**ጥላ መጽሔት**



## የአድራሻ ለውጥ



ጥላ መጽሔት የአድራሻ ለውጥ አድርጋለች። ለውጡ ግን የጎዳናው ስምና የቤት ቁጥሩ ብቻ ነው።ስለዚህ ከሚቀጥለው እትም ጀምሮ አስተያየቶቻችሁንና መልዕክቶቻችሁን በሚከተለው አድራሻ መላክ ትችላላችሁ።


**Mesfin Abraha**
**An der obergeis 1**
**36251 Bad Hersfeld**

# About Tila

Realizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

TILA is a political magazine published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany. Tila appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. **TILA** magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de, ethiopiazare.com and afroaddis.wordpress.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors. The articles which are posting here doesn`t represent the Magazine`s Editorial committee, rather the writers.

Don't take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today! We promise, you won't regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

**Tila Magazine is yours Magazine!**


## ውድ አንባብያን

**ጥላ** መጽሔት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መጹሔት ነው።መጽሔቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መጹሔት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መጽሔት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መጽሔቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመጽሔቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል። **ጥላ** መጽሔት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመጽሔቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መጽሔት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

**ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት!**



# EDITORIAL



## Reconciliation: Taking Nile as a Defining Cause

While the former secretary of state, Condoleezza Rice, explained on her infamous book "No Higher Honor" that why she kept the portrait of William Seward in her office she said Seward exploited the opportunity that was being created externally then bought Alaska from the Tsar of Russia; by then his measure didn't hold water. However five decades later while Russia became the power house of communism, by and large, Alaska was the buffer zone for the protection of the western hemisphere. Had it been belonged to Russia during the nuclear confrontation of cold war era, the world-today may not have same shape and form as present. History always commemorates Seward for his keen to exploit opportunities for national interest.

Obviously, for any state conducive environment, internal or external, could be precipitated sporadically. However, significant outcome will be achieved only if we successfully answer how far we exploited the available opportunity. For instance, due to the current global situation Ethiopia has become geo-politically pivotal and viable force of the region. Ethiopia is the key ally of the super power of our Planet.

The significance of these external opportunities in furthering our national interest and in heightening our stature on the international diplomatic arena is crucial. However, this by itself is not a sufficient condition to sustain as a functioning state, let alone as a viable regional force. We are not categorically sure that Ethiopia will be ended up into an imploded state due to the causative factor of internal problem than external threat in the foreseeable future.

We strongly believe in that Ethiopia must be redeemed by national reconciliation and political compromise. Many people hoped the Ethiopian millennium would be a good opportunity to do so; however, it was concluded simply by pardoning handful of political prisoners. We need not to wait other millennia to consider reconciliation again; Nile can be a good defining cause.

In principle, every Ethiopian believes in damming and utilization of river Nile. But the dissent rises as the TPLF regime uses the Nile dam project as a political tool to cover the looming internal problems.For we fail to compromise our differences, there is no complacent guarantee that those who have special interest on river Nile might make us to lose opportunities to further our national interest, if not they maneuver us to One-upmanship for good. In fact, those archenemies are working jointly in contrary to our interest by compromising their differences though they are entangled with periodically erupting problems.

We firmly urge that the TPLF led ruling party must give priority for national interest than blindly lone-chasing the miscalculated and nosedived journey; hence it has to plain the ground and call up all opposition groups for national consensus and reconciliation by taking Nile as a defining cause. Ethiopia needs super politicians like William Seward who keenly transform opportunities for sustainable national interest. we have more articles in this issue. we wish you a warm stay with TILA MAGAZINE.

**TILA MAGAZINE IS YOURS MAGAZINE!**



# ርዕሰ አንቀፅ



## አባይን ለእርቃችን መሠረት ብናደርገውስ?

"ኖ ሀየር ኦነር" በተሰኘው መፅሐፋቸው መግቢያ ላይ የቀድሞዋ የዩ.ኤስ. አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ካንደሊዛ ራይዝ በቢሯቸው የዊሊያም ሴዋርድን ፎቶ ለምን እንደሰቀሉት ሲያስረዱ *"ሴዋርድ በውጭ የተፈጠረውን አጋጣሚ ተጠቅም አላስካን ከራሽያው ንጉስ ገዛ። በወቅቱ ብዙም ትርጉም የሚሰጥ ጉዳይ አልነበረም ነገር ግን ከግማሽ ምዕተ አመት በኋላ ኮሚኒዝም ከራሽያ እየተነሣ የምስራቁን አለም ሲያጥለቀልቅ ብሎም በቀዝቃዛው ጦርነት የኒውክሌር ፍጥጫ ወቅት አላስካ የራሽያ ቢሆን ኖሮ ምናልባትም የዛሬው ዓለም መልክ በአሜሪካ ድል አድራጊነት አይመራም ነበር።ሴዋርድ አጋጣሚዎችን ለብሔራዊ ጥቅም በማዋል ታሪክ ሲዘክረው የሚኖር ፖለቲከኛ ነው"* በማለት ገልፀዋል።

እርግጥ ነው ውጫዊም ይሁን ውስጣዊ አጋጣሚዎች በተለያዩ ወቅቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ።ትርጉም ያለው ለውጥ የሚመጣው ግን የተፈጠሩትን አጋጣሚዎች ለዘለቄታዊ ሀገራዊ ጥቅም ምን ያህል ተጠቀምንበት የሚለውን በበቂ መመለስ ስንችል ነው።

ለምሳሌ አሁን ባለው አለማቀፍ ሁኔታ መሠረት ኢትዮጵያ በሁለት መልክ የአካባቢው ጂኦ-ፖለቲካዊ ቁልፍ ሀገር /Geo-politically Pivotal/ እንዲሁም የአካባቢው ወሳኝ ኃይል /Viable Force/ መሆን ችላለች።በአለማቀፍ የፀረ-ሽብር ትግል ውስጥ ኢትዮጵያ የልዕለ ኃያሏ ሀገር አሜሪካ ቁልፍ አጋር ስትሆን በአፍሪካ-ቻይና የኢኮኖሚ ትስስር ውስጥም እንዲሁ ኢትዮጵያን የሌላኛዋ ኃያል ሀገር ቻይና ወሳኝ አጋር አድርጓታል።እነዚህ በውጪ የተፈጠሩ መልካም አጋጣሚዎች ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን ወደፊት ለማስቀጠል እንዲሁም በአለማቀፍ የዲፕሎማሲው መስክ ተሰሚነታችንን ከፍ የሚያደርጉ መሆናቸው አሌ የማይባል ሀቅ ነው።ይሁን እንጂ ይህ በራሱ በቂ ነው ማለት አይቻልም።የአካባቢው ወሳኝ ኃይል ሆኖ ለመቆየት ብቻ ሳይሆን እንደሀገርም ለመቀጠል የውስጥ ችግሮቻችን እልባት ሊያገኙ ይገባል።ከውጭ ከሚመጣ አደጋ ይልቅ ከውስጥ በሚመጣ አደጋ የተዳከመች አልያም የተበታተነች ኢትዮጵያ እንደማትኖር ደፍሮ መናገር ከሚከብድበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።

በአንድ ነገር አጥብቀን እናምናለን፦ ሀገራችን በብሔራዊ እርቅ እና በፖለቲካ መቻቻል መዋጀት አለባት። ይህን ለማድረግ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ጥሩ አጋጣሚ ይፈጥራል ተብሎ በበርካታ ወገኖች ተጠብቆ የነበር ቢሆንም እስረኞችን ከመፍታት በዘለለ የተጠበቀው ሳይሆን ቀርቶ ችግሮቻችንም እየበረቱ ይገኛሉ። ይህን ሃሳብ ደግሞ ለማሰብ ሌላ ሚሌኒየም መጠበቅ አያስፈልግም።አባይን የመነሻ ሀሳብ ማድረግ በቂ ነው።

በመርህ ደረጃ አባይ እንዲገደብ ብሎም ለተለያዩ ልማቶች እንዲውል የማይመኝና የማይፈልግ ጤነኛ ኢትዮጵያዊ አይኖርም።ችግር እየተፈጠረ ያለው የወያኔ መንግስት የአባይን ግድብ ፕሮጀክት እንደ አንድ የፖለቲካ መሣሪያ በመጠቀም ውስጣዊ ችግሮቹን ለመሸፈን ሲጥር መታየቱ ነው።


ነገር ግን እዚያም ሳይደርስ በአባይ ውሃ ላይ የተለየ ፍላጎት ያላቸው ኃይሎች ውስጣዊ ችግሮቻችንንና ማቻቻል ያቃተንን ልዩነቶቻችንን በመጠቀም ብሔራዊ ጥቅማችንን ማሳጣት ብቻ ሳይሆን በውጪ የተፈጠሩልንን አጋጣሚዎች ሳይቀር መጠቀም በማንችልበት ደረጃ ወደ ታች እንደማያወርዱን ዋስትና የለንም።እነዚህ ኃይሎች ምንም እንኳን በየጊዜው እያገረሸ ባለ የውስጥ ችግር የተተበተቡ ቢሆንም ዛሬም ድረስ በአባይ ጉዳይ ልዩነቶቻቸውን አቻችለው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም በተፃራሪ እየሰሩ ይገኛሉ።

በትረ-መንግስቱን የጨበጠው የወያኔ መንግስት ለፓርቲው ፖለቲካዊ ትርፍ ተብሎ በተሳሳተ መልኩ ከተሰላ የተናጠል የቁልቁለት ጉዞ ይልቅ ዘለቄታ ላለው ብሔራዊ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ከሚሉ ወገኖች  ሁሉ ጋር ብሔራዊ መግባባትንና እርቅን የሚያደርግበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፤ለዚህም አባይን እንደ አንድ መነሻ አድርጎ መውሰድ የወቅቱ አማራጭ መንገድ ሊሆን ይችላል እንላለን።

ዛሬ ኢትዮጵያ ልክ እንደ ዊልያም ሴዋርድ ሁሉ የተፈጠሩትን መልካም አጋጣሚዎች በፍጥነት ዘላቂነት ላለው ብሔራዊ ጥቅም የሚያውሉ ፖለቲከኞችን አጥብቃ ትሻለች። ጥላ መጽሔት በአባይ ግድብና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ሽፋን ይዛ ለንባብ በቅታለች።መልካም ቆይታ ከጥላ መጽሔት ጋር- ምኞታችን ነው!

**ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት! ”ጥላ የሚያነቧት ብቻ ሳትሆን የሚፅፉባትም መጽሔት ናት”**

## Ethiopia`s Electi- on ! Before and after the election




## "It's injustice that motivates us to do something, to take risks, knowing that if we don't, things will remain the same".

Digna Ochoa (1964-2001)




**Digna Ochoa was a human rights lawyer in Mexico. She was born May 15, 1964 in Misantla, the state of Veracruz. Assassinated: October 19, 2001**

# አባይ ሊያለማን ወይስ ሊያጠፋን?

## የሕዳሴው ግድብና ዐባይ፤ የሚሊኒየሙ ዐባይ ተጋቦት

/sela abbomssa abbom-ssa@gmail.com/

*አዘጋጅ ለኢትዮጵያ ፍቅር ከቃሊቲ*

**የዐባይ ሥረ_መሠረትና የሕዳሴው ግድብ ማነጣጠሪያ እነሆ!**

ጥናቱ የተፈጸመው ሚያዚያ 2003 (2011 እ ኤ አ) ነው።

አቅርቦት የፀሐፊው ትክክለኛ ቅጂ (በአቀራረባዊ ጥንቅር)

**መነሻ**

የጊዜው የኢትዮጵያ ጉዳይ ሆኖ የቀጠለውና ሕዝቡም የጠየቁትን እያደረገ ያለበት የሚሌኒየሙ ታላቅ የዐባይ ግድብ እንደተነገረው፤ የሚገደበው ከሱዳን ድንበር 17 (አሥራ ሰባት) ኪሎሜትር ባለ ቀረቤታ በዐባይ ወንዝ ላይ ነው።

ግድቡ ወደ 62 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ የመያዝ አቅም አለው። የውኃው መጠን የጣና ሐይቅ ከሚይዘው ውኃ እጥፍ ይሆናል።

በሚታቆረው ውኃ 6ሺ (ስድስት ሺ) ሜጋ ዋት የኤሌትሪክ ኃይል ሊመረት ታቅዷል። የሚመረተው የኤሌክትሪክ ኃይል ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሱዳንና ለግብፅም ሊሸጥ ታስቧል። ይህ ግንባታ 80 ቢሊዮን ብር ይፈልጋል።

ገንዘቡ በግብፅ ተፅዕኖ ሳቢያ የውጭ ብድር ወይም ዕርዳታ እንዳያገኝ ስለተደረገ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ የመዋጮና ቦንድ ሺያጭ ሊሸፈን ተወስኗል።ለሕዝቡም ታሪካዊ ተዐምር ሊሠራ እንደሆነና የልማት ሁሉ አንጋፋ እንደሆነ ተነግሮት የቻለውንና ያልቻለውንም ከማድረጉ በላይ ለሃገር የሚበጅ ልማታዊ ድንቅ እንደተፈጠረ ተበስሮለታል።

ባለፈው ሚያዚያ (April) 2013 እ ኤ አ ወር ማብቃያ አካባቢ በወጣው ዜና ደግሞ (ይህ ጥንቅር ከቀረበ ከሁለት ዓመት በኋላ መሆኑ ነው። ቻይና ለሚሌኒየሙ ግድብ ግንባታ 1.5 ቢሊዮን ዶላር ልታበድር ነው ተብሏል።

# ታዲያ ግብፅና ሱዳን ምነው ዝም አሉ?

እኮ ቢጠቅማቸውማ ነው ዝምታቸው፤ የዐባይ ልጅ ይህ እንዴት ያየዋል? አባይ (ናይል)እየተባለ የሚጠራው በዓለም ረዥሙ ወንዝ፣6671 ኪሎ ሜትር እርዝማት ሲኖረው፣ከዘጠኝ አገሮች ይመነጫል።ግብፅ ምንም የምታመነጨው የውኃ አስተዋፆ የላትም። ሆኖም በናይል ውኃ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ አገር ናት። ግብፅ 100% የሰሐራ በረሃ አካል በመሆኗ በሜዲቴሪንያን አካባቢ ጥቂት ዝናብ ጠብ ከማለቱ ሌላ ከዓመት ዓመት ዝናብ አይጥልም።

በሌላ በኩል ደግሞ ከሁሉም የናይል ተፋሰስ አገሮች ይበልጥ የ80% በመቶ ከአባይና ከሌሎች የኢትዮጵያ ወንዞች የሚገኘው ውኃ አባይን ይገልጸዋል። በጠቅላላው የናይል ወንዝ 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ በዓመት ሲሰጥ ከዚህ ውስጥ ከኢትዮጵያ የሚገኘው የውኃ ድርሻ መጠን 54 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ ነው። የዚህ ሁሉ ውኃ ምንጭ ኢትዮጵያ



ስትሆን፤እንደ ሱዳንና ግብፅ እምነት ጥቂት ውኃ እንኳን ለመጠቀም መብት የላትም።ሌሎቹንም የናይል ውኃ አመንጪና ባለቤት የራስጌ አገሮችን በማግለል መብታቸውን ገፍፈው ሱዳንና ግብፅ ተከፋፍለውታል።

እ ኤ አ 1959 ዓ ም በተፈራረሙት ስምምነት መሠረት ግብፅ 55.5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ፤ሱዳን ደግሞ 18.5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ ይወስዳሉ።በተለይ ግብፅ የውኃው ዋና ባለቤት እራሷን አድርጋ በመቁጠር አመንጪዎቹን የራስጌ አገሮች ለአነስተኛ የውኃ ጠቀሜታ እንኳን ፈቃጅ መሆን አለብኝ ባይ ናት። ለዚህም ኢትዮጵያን ማዳከም ወይንም ማጥፋት ተልዕኮዋ ሆኗል።

### የአባይ ጠቀሜታ


ግብፅና ሱዳን ፍፁም ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፤ በተቃራኒው የውኃ መነሻ የሆነችው ኢትዮጵያ ተጠቃሚ አልሆነችም።

ግብፅ 3.0 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ታለማለች።

ሱዳን 1.8 ሚሊዮን ሄክታር እንደዚሁ በናይል መስኖ ታለማለች።

***ኢትዮጵያ አትጠቀምም በመስኖ አለማችም።***

የግብፅ በረሃ በናይል ውኃ በሺ ዓመታት የሚቆጠር የመስኖ እርሻ ልምድ ለምቶ እራሳቸውን ከመመገብ አልፈው የዳበረ ኢኮኖሚ ገንብተውበታል። አባይን ወደ ምዕራብ የግብፅ በረሃ ቀይሰው በመውሰድ ተጨማሪ 1.2 ሚሊዮን ሄክታር በረሃ ለማልማት መንቀሳቀስ ከጀመሩ ቆይተዋል።በዚህ ምዕራባዊ ከተማ ከአንድ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚኖርበት ዘመናዊ ከተማ እየተገነባ ነው። የሲናይንም በረሃ ለማልማት በዓመት 4.5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ የአባይ ውኃ የሚያስተላልፍ ቧንቧ ዘርግተዋል። የመስኖ ሥራቸውን ለማካሄድ ያስቻላቸውም ታላቁ የአሳዋን ግድብ ነው።ግድቡ 162 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ የማከማቸት አቅም አለው። በክረምት ወራት ከኢትዮጵያ የሚፈሰውን ውኃ አጠራቅመው በመያዝ በሰከንድ 1500 ቶን ውኃ እየለቀቀ በረሃውን ያለማል። ይህም ሆኖ በግብፆች ዕቅድ ተጨማሪ በረሃ ለማልማት 15ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ ተጨማሪ ያስፈልገዋል። ለዚህም የተለያዩ ፕሮጀክቶች አስጠንተዋል። ጥናቱ ተጠናቆ ግንባታውም ተጀምሮ የነበረው አንዱ




ፕሮጀክት በደቡብ ሱዳን ክልል ያለው የጀንገሌ ካናል ፕሮጀክት ነበር። የናይል ወንዝ በደቡብ ሱዳን ሱድ እየተባለ የሚጠራውን ረባዳና ረግረግ ሰፊ መሬት አቋርጦ ያልፍል።ወንዙ በክረምት ከአፍ እስከ ገደብ ሲሞላ ግደቡን ጥሶ ለጥ ወዳለው ሜዳ መፍሰስ ይጀምራል።ግድቡን አልፎ የተንጣለለው ውኃ ተመልሶ ወደ ወንዙ ሊገባ ስለማይችል፤እንደተንጣለለ ይደርቃል።ይህም በፀሐይ ሙቀት እየተነነ ይጠፋል። ታዲያ ግብፃውያን የጀንግሌ ካናልን ፕሮጀክት ያጠኑትና ሥራውንም የጀመሩት በትነት የሚባክነውን ውኃ በማግኘት የናይልን ውኃ መጠን 10% ከፍ ለማድረግ ነበር።

1ኛ የጀንግሌ ካናሉ ግንባታ የተጀመረው የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ድርጅት የነፃነት እንቅስቃሴ በጀመረበት ወቅት ስለነበር ፕሮጀክቱ ሳይገፋ አገራችን ይደርቃል፣ ኢኮሎጂውም ይለወጣል፣ በማለት ኤስ .ፒ .ኤል. ኤም ፕሮጀክቱ ላይ ጥቃት በመሰንዘር አጨናገፈው።

2ኛ ተጨማሪ ውኃ ለማግኘት ያስችላል ተብሎ የተጠናው ሌላው ፕሮጀክት ደግሞ በኢትዮጵያ ትልልቅ ግድቦች መገንባትና የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ነው። ግብፅ በረሃማ አገር በመሆኗ የፀሐይ ሙቀት ያጠቃታል፤በዚያ የተነሣ በአገራቸው ከተገነባው ቃላቁ የአስዋን ግድብ በፀሐይ ሙቀት ብቻ በትነት ከተከማቸው ውኃ 12% ይባክናል።ይህ በጣም የሚያሳስባቸው ጉዳይ ነው። ብዙ ውኃ ሊይዝ የሚችል ሌላ ትልቅ ግድብ ለመገንባት የሚቻለበት ቦታ ስለሌላቸው ተጨማሪ ውኃ በሃገራቸው ውስጥ ለማከማቸት ያላቸው ዕድል በጣም የመነመነ መሆኑን ተረዱት። በዚህ የተነሣ ጥረታቸውን በኢትዮጵያ ላይ አድርገዋል።በደጋው ኢትዮጵያ ትላልቅ ግድቦች ለገነቡባቸው የሚችሉበት ቦታዎች በርካታ ናቸው። በሚገደቡት ግድቦች የሚከማቸው ውኃ በትነት የመባከን አደጋ አያጋጥመውም።ውኃው ሳይባክን ለብዙ ጊዜ ተጠብቆ የመቆየት ዕድል አለው።ኤሌክትሪክ ለማምረት እየተባለ ከሚገነቡት ግድቦች ከሚለቀቀው ውኃ ምን ያህል ተጨማሪ ውኃ ሊገኝ እንደሚችል ግብፃውያን አስጠንተው አውቀውታል።

በጥናቱ መሠረት በኢትዮጵያ 23 ትላልቅ ግድቦችን በአባይ መጋቢ ወንዞች ላይ መገንባት የሚቻልባቸው ቦታዎች ተለይተው ታውቀዋል፤መነሻ ጥናት ተካሄዶባቸዋል፤እንደጥናቱ በእነዚህ ቦቻዎች በሚገነቡ ግድቦች ብዙ ቢሊዮን ሜትር ኩብ መጠን ያለው ውኃ ይከማቻል።ከዚያም በያንዳንዱ ግድብ የሚተከሉት የኤሌክትሪክ ማመንጫ ተርባይን ለማሽከርከር ውኃ ይለቀቃል።የአባይ ወንዝ በሚሞላበት ወቅት የአገራችንን ድንበር አልፎ ሱዳን ሲገባ የሚያፈሰው የውኃ መጠን 400 ሜትር ኩብ ውኃ በሰኮንድ ሲሆን አባይ ደረቀ በሚባልበት በበጋው ወቅት ደግሞ 4 ሜትር ኩብ ውኃ በሰኮንድ ይፈሳል። ልዩነቱን አጢኑት በበጋው የሚፈሰው በአንድ መቶ ጊዜ ይቀንሳል።ከዚህ ሁኔታ መገንዘብ የሚቻለው በሱዳንም ሆነ በግብፅ በክረምት ወራት ከኢትዮጵያ የሚፈስላቸውን ውኃ ገድበው በመያዝ በበጋ ወራት እየለቀቁ መጠነኛ የእርሻ ሥራ ከማካሄድ ውጭ የመስኖ እርሻ እንቅስቃሴ አያካሄዱም ማለት ነው። **በኢትዮጵያ ግድቦች ተገንብተው ውኃ እየለቀቁ ተርባይኖችን ማሽከርከር ሰንጀምር ግን ይህ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ይለወጣል። ከተጠኑት 23 የግድብ ሥፍራዎች ውስጥ አነስተኛ ውኃ የማከማቸት አቅም ያላቸው አራት ግድቦች ቢገነቡና በየአንዳንዱ ግድብ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት፤ አራት አራት ተርባይኖች ቢተከሉና እነዚህን ተርባይኖች ለማሽከርከር 20 ሜትር ኩብ ውኃ በሰኮንድ ቢለቀቅ ሱዳንና ግብፅን አባይ ሲደርቅ 80 ሜትር ኩብ ውኃ በሰኮንድ ያገኛሉ ማለት ነው።**

ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ብቻ ለማምረት ፈልጋ ግድብ ከገደበችና ተርባይኖችን ለማሽከርከር አንድ ጊዜ ውኃ መልቀቅ ከጀመረች በኋላ ውኃውን በከፊል ወይም በሙሉ ለመስኖ እርሻ ልማት መጠቀም ብትሞክር የሱዳንና የግብፅን ሕዝቦች በረሃብ ፈጀች፤ የአባይን አቅጣጫ ቀየረች፤ በሚል ሰበብ ለጦርነት መነሳታቸው አይቀርም። በዓለም አቀፍ ደረጃም እንድትወገዝ ፓለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ጫና እንዲወድቅባት ያደርጋሉ።

በዚህ ምክንያት በአባይ ወይም በአባይ ገባር ወንዞች ላይ ግድብ ገንብተን የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ከመጀመራችን በፊት ውሎ አድሮ ኢትዮጵያን የሚጎዳ ሁኔታ አለመፍጠሩን ከብዙ አቅጣጫዎች መመርመር አለብን። እንደሚታወቀው የኤሌክትሪክ ኃይል ለማንኛውም አገር ዕድገትና ሥልጣኔ ወሳኝ ኃይል ነው። ኃይል እንደመሆኑ ሁሉ ኢትዮጵያም የኢሌክትሪክ ኃይል በከፍተኛ ደረጃ ያስፈልጋታል። በቀላል መንገድ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማግኘት ደግሞ ያላትን የውኃ ኃይል መጠቀም ይኖርባታል። በውኃው ኃይል **ኤሌክትሪክ ስናመርት ግን ተርባይኖቹን የሚያሽከረክረው ውኃ ተለቆ የሚሄድ ሳይሆን ለመስኖ ልማት ላይ መዋል ይኖርበታል።ግድብ ፣ገድበን ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ስናስብ፣ የሚለቀቀው ውኃ እታች ወርዶ ማሳውን እንዲያጠጣ ተደርጎ መታቀድ ይኖርበታል።በዚህ አኳኋን ካልታቀደ በከፍተኛ ወጪ ያጠራቀምነውን ውኃ ያለምንም ክፍያ ለሱዳንና ለግብፅ አሳለፈን ሰጠን ማለት ነው።** ከዚህ ግንዛቤ በመነሣት በደርግ ጊዜ የመልካ ዋከና የኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያ ሲገነባ በተጓዳኝ በኡጋዴን ጎዴ አካባቢ ተርባይኑን ለማሽከርከር የሚለቀቀው ውኃ ተጠልፎ እስከ 50ሺ ሄክታር የመስኖ እርሻ እንዲያጠጣ ታቅዶ ኤሌክትሪክ ማመንጨት ሥራ እንደጀመረ የ20ሺ ሄክታር ማሳ እንዲያለማ ተደርጎ ነበር።

በሌላ በኩል ከልማት ጋር ሣይያያዝ የተገነባው የፊንጫ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያ የሚለቀቀው ውኃ ያለጥቅም መፍሰሱን በመመልከት ለስኳር ፋብሪካ ጥሬ ዕቃ የሚሆን ሸንኮራ አገዳ በ10ሺ ሄክታር ማሳ እንዲያለማ ታቅዶ ሥራው ተጀምሮ ነበር።የጣናን ሃይቅ በማሳደግ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ሲወሰን በተመሳሳይ መንገድ የሚለቀቀውን ውኃ በመጠቀም በበለስ ሸለቆ እስከ 100ሺ ሄክታር የመስኖ እርሻ ለማት ለማካሄድ እንቅስቃሴው ተጀምሮ ነበር።በሌሎች አካባቢዎችም የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት በሚታሰብበት ጊዜ

የሚለቀቀው ውኃ ጥቅም ላይ ውሎ የአገራችንን ኤኮኖሚ ለማሳደግና በምግብም ራሳችንን እንድንችል እንዲረዳ ጎን ለጎን መታቀድ ነበረበት።

ከመስኖ ልማት ጋር ሳይያያዝ ግድብ መገንባትና ኤሌክትሪክ ማመንጨት የግብፅን ፍላጎት በፍቃደኝነት ማሟላት ማለት ነው።ግብፅ ሙሉ ወጪውን በመሸፈን በኢትዮጵያ ትላልቅ ግድቦችን ለመገንባት የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት የሚለቀቀውን ውኃ ሳይቀናነስ እንድትወስድ ማረጋገጫ ቢሰጣት ያለ ማቅማማት እንደምትስማማ በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል።ግብፅ ውኃውን ከምንም ነገር አስበልጣ ስለምትፈልገው በኢትዮጵያ ግድቦች ቢገነቡና ኤሌክትሪክ በቻ እንዲመረት ቢደረግ ምንም ዓይነት ተቃውሞ አታሰማም።ለማስረጃ ያህል በጣና ሃይቅ የአባይ ወንዝ መውጪያ ላይ የተወሰነ ግድብ ተገንበቶ የጣና ውኃ መጠን እንዲጨምር ከተደረገ በኋላ በምዕራብ አቅጣጫ ጣና ተሽነቁሮ ውኃውን ቁልቁል በመልቀቅ ተርባይን እንዲያሽከረከር ተደርጎ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ከተጀመረ ቆየት ብሏል፤ የተከዜ ወንዝ ተገድቦ የተጠራቀመው ውኃ እየተለቀቀ ኤሌክትሪክ ማምረት ከተጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል።ታዲያንስ ግብፆች የተጠራቀመ ውኃ በጣም በሚያስፈልጋቸው በድርቅ ጊዜ ሳይቋረጥ የሚያገኙት መሆናቸውን ስለሚያውቁ ለምን በጣና ሃይቅ ኤሌክትሪክ ይመረታል፣በተከዜ ወንዝ ላይ ግድብ ተገንብቶ ኤሌክትሪክ ማመንጨት ለምን ተጀመረ ጥቅማችንን ይጎዳል ብለው አልተናገሩም ፤ ተቃውምም አላሰሙም፤ ምክንያቱ ተጠቃሚዎቹ እነሱ ናቸውና።

አባይን አስመልክቶ ይህን ያህል ከተነጋገርን ስለ" ታላቁ የሚሊኒዮም ግድብ" አንዳንድ ነገር ብናነሳ መልካም ይመስለኛል።እንደተነገረን ግድቡ የሚገነባው በቤኒሻንጉል ክልል ከሱዳን ድንበር 17 ኪሎሜትር ርቀት በሚገኝ ቦታ ላይ ነው። ግድቡ 62 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ ይይዛል።የግንባታው ወጪ 80 ቢሊዮን ብር ሲሆን በኢትዮጵያ ሕዝብ መዋጮ ይሸፈናል ተብሏል።በግድቡ ውኃ ከ6ሺ በላይ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ይመነጫል።እንግዲህ ከግድቡ ኢትዮጵያ የምታገኘው ጥቅም የኤሌክትሪክ ኃይል ብቻ መሆኑ ነው።ግብፅና ሱዳን ግን ተጨማሪ ውኃ ያገኛሉ። ኤሌክትሪክ ኃይል ለማምረት ምን ያህል ተርባይኖች እንደሚተከሉ አይታወቅም።

6000ኪሎ ዋት ኤሌክትሪክ ለማምረት አንዱ ተርባይን 50 ሜጋ ዋት የሚያመነጭ ቢሆን እንኳን ከ 100 ተርባይኖች በላይ መተከል ይኖርባቸዋል።አንዱን ተርባይን ለማሽከርከር 5 ሜትር ኩብ ውኃ በሰኮንድ መልቀቅ ያስፈልጋል ቢባል እንኳን 100 ተርባይኖችን ለማሽከርከር 500 ሜትር ኩብ ውኃ በሰኮንድ መልቀቅ ያስፈልጋል ማለት ነው። አባይ ሲሞላ በክረምት ወራት ከተጠራቀመው ውኃ ተርባይኖችን ለማሽከርከር መልቀቅ አስፈላጊ አይሆንም። ወንዙ በግድቡ ላይ ሰለሚያልፍ እግር መንገዱን ተርባይኖቹን እያሽከረከረ ያልፋል።በግድቡ የተከማቸውን ውኃ መልቀቅ የሚያስፈልገው በበጋ ወራት አባይ ሲደርቅ ነው።ተርባይኖች ከዓመት ዓመት መሽከርከር ሰለአለባቸው ከግድብ እየተለቀቀ የሚወርደው ውኃ በቋሚነት ያስፈልጋል። በዚህ አሠራር በክረምት ወራት አባይ ሲሞላ ከሚገኘው የውኃ መጠን የበለጠ ግብፅና ሱዳን በበጋ ወራት ያገኛሉ ማለት ነው።ይህ መጠን በተፈጥሮ ከሚያገኙት በእጅጉ ይበልጣል።በተፈጥሮ የሚያገኙት ውኃ እየቆጨን እያለ እያንዳንዱ እትዮጵያዊ እየተመጠጠ በተሰበሰበው ገንዘብ ትልቅ ግድብ ገድበን ውኃ አጠራቅመን በተጨማሪ መስጠታችን እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተረዳው ወይም የተገነዘበው አይመስልም።ሕዝቡ የሚመስለው ወንዙ ተገድቦ ለልማት ውሎ ከረሃብ እንደሚወጣ ነው።

በጥቅሉ አባይ ሊገደብ ነው እየተባለ ይነገረዋል።በሚገደበው ግድብ ከሚከማቸው ውኃ አንድ ሄክታር መሬት እንኳን በመስኖ እንደማይለማ አይነገረውም። ከታላቁ ግድብ ጋር ምንም የመስኖ ልማት ፕሮግራም አልተያዘም። ወደፊት ውኃውን ለልማት እናውለዋለን እንዳይባል ከግድቡ በታች ለእርሻ የሚሆን መሬት የለም። በርባራ አካባቢ ነው፤ ከዚያም ቢሆን ውኃው ተለቆ ተርባይን ከአሽከረከረ በኋላ በቀጥታ ሱዳን ውስጥ ይገባል።ምክንያቱም በሱዳን ጠረፍና በግድቡ መሐል 17 ኪሎ ሜትር ብቻ እርቀት ነው ያለው።የውኃ ጉዳይ ለግብፅ የመኖር ወይም ያለመኖር ጥያቄ ነው። ከኢትዮጵያ የምትወጣዋን ውኃ ትቆጣጠራለች። ይህ አዲሱ ግድብ ሥራው ተጠናቆ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ውኃ መልቀቅ ከጀመረ በኋላ ውኃውን ማቆም አይቻልም።ምክንያቱም ከዓመት ዓመት የሚፈሰው ውኃ እየተለካ ይመዘገባል።

ኤሌክትሪክ ማምረት አቆማለሁ ብላ ኢትዮጵያ ብታቆም ጦርነት እንደማወጅ ተቆጥሮ በግብፅና ከሱዳን ጋር ውጊያ መግጠምን ያስከትላል።በመሆኑም ዛሬ የሐገር ፍቅር ስሜታችንን ቀስቅሰው በሚገባ ግልፅ ሳይሆንልን የግድቡን ሥራ መደገፋችን ገንዘብ ማውጣታችን ወደፊት መዘዝ ያስከትልብናል። 'አባይ ሊያለማን ወይስ ሊያጠፋን' ብለን መጠየቅም ይኖርብናል። ግድቡ የመስኖ ልማት ጋር ቢያያዝ ከረሃብ ከድህነት ልንወጣ ስለምንችል ማንኛውንም ዓይነት መስዋዕትነት ሕዝብ ቢከፍል ተገቢ በሆነ ነበር፤ ከሕዝብ ጎን ጋር ያልተዛመደ ግዙፍ ሥራ መወጠኑ በኋላ አሁን ለሚደረገው የሚያስጠይቅ ሊሆን ይችላል።

የሚገርመው ደግሞ ከዚህ ድንቅ ከተባለው ግድብ የሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል ለሱዳንና ለግብፅ ይሸጣል መባሉ ነው።የሚሸጠውም በጣም በአነስተኛ ዋጋ ነው።በአሁኑ ጊዜ ለሱዳን አንድ ኪሎዋት የሚሸጠው በስድስት ሳንቲም የአሜሪካን ሲሆን፣ሱዳን በሃገሯ እስከአሁን የምትሸጠው ሃያ ስድስት ሳንቲም የአሜሪካ ነው።በዚህ ዓይነት የ ሃያ ሳንቲም ትርፍ ታገኛለች ማለት ነው።

ሱዳንና ግብፅ በውኃችን የተነሣ ጠላት አድርገውን ብዙ ጎድተውናል።ወደፊትም ይጎዱናል። ሃገራችንን ለመከፋፈልና ለመገነጠል ለተሰለፉት ዛሬ ኤርትራን ገንጥለው ለሚያስዳድሩትና የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር በጎሣ ከፋፍለው ለሚመሩት ቡድኖች አጋር ሆነው ቆይተዋል።'አንዳንዴ የአባይ ግድብ ለነዚህ ሃገሮች ወሮታ ይሆን' ብለው የሚጠይቁ ሃገር ወዳዶች አሉ። ታዲያ በዚህ የጠላትነት መንፈስ እየተመለከቱን እያሉ ኤሌክትሪክን ያህል የልማት ኃይል አቅራቢ ሆነን እንዲያድጉና እንዲበለጽጉ በወታደራዊ ቴክኒክና ቴክኖሎጂ እንዲዳብሩ መርዳታችን እንደሆነ መገንዘብ አልቻልንም።

ኤሌክትሪክ ለጎረቤት አገሮች የመሸጥ ሐሣብ በደርግ ዘመን ተነስቶ ነበር።የጦር መሣሪያ ከማስታጠቅ አይተናነስም ተብሎ ሐሣቡ ውድቅ ተደርጎ ነበር።ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን የኤሌክትሪክ ኃይል ከሌሎች ወንዞች ማመንጨት ይቻላል ተብሎ፤በግልገል ግቤ በርካታ ግድቦች ተገድበው በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚመረትበት ቦታ የሌለ ይመስል ታላቁ ግድብ ኤሌክትሪክ በኤሌክትሪክ ያደርገናል ችግራችን በሙሉ ይወገዳል፤እየተባለ የሚካሄደው አዳናጋሪ ፕሮፓጋንዳ ወደፊት ሃቁ መታወቁ አይቀርም።እኔ እንደምገምተው ከግብፅ ጋር ስምምነት አድርገው በጋራ የነደፉት ፕሮጀክት ይመስለኛል።በጥናቱም ላይ የግብፅ እጅ ይኖርበታል የሚል ግምት አለኝ።የዚህ ግድብ ሥራ ግብፅን የሚጎዳ ቢሆን ኖሮ በዓለም ከፍተኛ ጩህትና የፖለቲካ ትረምስ ይሰማ ነበር። ግብፅ ያለችው ነገር ቢኖር ቴክኒካል ወረቀቶቹን ስጡኝ ነው፤ይህም ለማለት ያህል እንጂ ቴክኒካል ጥናቱ ቀድሞ በእጇ ይገኛል። አሁን ለግብፅና ለሱዳን የሚጠቅም ሥራ ኢትዮጵያ በማንቀሳቀሷ ከዚህ በፊት በአባይ ጉዳይ ላይ አልነጋገርም፤ ስምምነትም በአዲስ መልክ አላደርግም ሲሉ የነበሩ ሁለቱ አገሮች በጉዳዩ ላይ እንደራደራለን የሚል አቋም ይዘዋል።የኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ ማውጣቱን እንዲቀጥል ብቻ አለፍ አለፍ እያሉ በለሆሳስ የግድቡ ሥራ አሳስቦናል ይላሉ።

ዘለዓለማዊ የሃገር መታደግና ዕድገት ሳይሆን ዘለዓለማዊ ጠንቅ እንዳይተከልባት ለምን? ለማን? እንዴት? የሚለው የሃገር ጥቅም መለኪያ፣ሊተኮርበት ይገባል።ከራስ እያወለቁ ጠላትን እያስታጠቁ ግንባታ ስንኩል ስለሆነ አባይ መዘዝ ሳይሆን ሕዝብ አገዝ እንዲሆን ሁሉም ዕድሉ አሁን መሆኑን መገንዘብ ይገባዋል።

# ጨቋኙን ሥርዓት በቃህ ልንለው ይገባል።

**Tadesse Alemu /Hof**

ዘረኛው እና አምባገነኑ የወያኔ መንግስት ሀገራችንንና ወገናችንን አሸማቆ መግዛት ከጀመረ እነሆ ከሁለት አስርት አመታት በላይ አስቆጥሯል።ይኸው የወያኔ አምባገነን ዘረኛ መንግስትና ሥርዓቱ የፈጠረው የኢኮኖሚ ድቀትና የዘር ጭፍጨፋ ውጤት ዜጎች ሀገራቸውን ለቀው በባህር ማዶ እንዲንከራተቱ አድርጓል።

ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ መብትን መጠየቅ በሽብርተኝነት የሚያስፈርጅበት የገዢው ፓርቲ አባል ካተሆነ በቀር የመማርና ሰርቶ የማደግ መሰረታዊ የዜጎች መብት የተነፈገበት ሁኔታ ተንሰራፍቶ ይገኛል።በዚህ አምባገነን የወያኔ ሥርዓት ምክንያት ዜጎች ሀገራቸውን እየወደዱ ለሀገራቸው ማበርከት ያለባቸውን አስተዋጽዖ ሳያበረክቱ መቅረቱ ገና ከጅምሩ ወያኔ የቀየሰው ሀገርን በቋንቋ ፣በብሄርና በዘር የመከፋፈል ፕሮግራም መሆኑ ግልጽ ነው።አገራችን ከጥንት ጀምሮ የባህል ቁርኝት የጠበቀባት፣የሀይማኖቶች መከባበር ያለባት የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች ሀገር እንደመሆኗ መጠን ብሄሮች ተከባብረው የሚኖሩባት ሀገር መሆኗ እየታወቀ ክልሎችን በመልክዓ ምድር አቀማመጣቸው መከለል ሲቻል ከግለሰብ መብት ይልቅ የቡድን መብት ይቀድማል በሚል ተራ አመክንዮ ብሄርን ከብሄር በማጋጨት የግለሰብን መብት በመደፍጠጥ የሚቃወሙትንም በማፈን እና በማሰር ወያኔ ድርጊቱን ቀጥሎበታል።

አፋኙ የወያኔ መንግስት መሰረታዊ የዜግነት መብት የሚጠይቁ ዜጎችን የሽብርተኝነትና የፀረ-ህገ መንግስት ስያሜ በመለጠፍ ለወያኔ ካድሬዎች ሥራ ማስፈፀሚያ ብር ያልሰጡትን ባለሀብቶች ልማታዊ ያልሆኑ ባለሀብት ወይም ፀረ-ልማት በማለት ህዝቡ ሀገሩንና የትውልድ ቦታውን እንዲጠላ አድርጎታል።ስለሆነም ሀገራችንን ከአፈና አገዛዝ ቀንበር ነፃ ለማውጣት በህብረት እና በፅናት መቆም ይኖርብናል።

# ስቃይና እንግልት ያልገታው ስደት ቀጥሏል!

**Wengel Amen Dawit/Nürnberg**

የኢትዮጵያ ወጣቶች ወደውና ፈቅደው ከሚሄዱባቸው፣ ነገር ግን ሰብአዊ መብቶቻቸው ከሚጨፈለቁባቸው አገሮች ውስጥ በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙት የዓረብ አገሮች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ስደትን አስመልክቶ በቅርቡ ካቀረባቸው ጥናቶች ውስጥ አንዱ እንደሚያትተው፣ ኢትዮጵያውያን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ መሰደድ ከጀመሩ 35 ዓመታት ገደማ ይሆናቸዋል፡፡

ዛሬ ላይ ግን ይህ ታሪክ ተቀይሮ ከመላ አገሪቱ የሚንቀሳቀሱት የስደተኞቹ ቁጥር እጅግ አሻቅቧል፡፡ ሁኔታው ግራ የሚያጋባም እየሆነ መጥቷል፡፡ ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2005 ዓ.ም. ድረስ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ፈቅዶና መዝግቦ የሄዱ የሠራተኞች ቁጥር ከ200 ሺሕ በላይ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ከ80-98 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡

ኢትዮጵያውያን ከመቼውም በላይ በተበራከተ ቁጥር ወደ መካከለኛው ምሥራቅ መጉረፍ የጀመሩት በ2003 ዓ.ም. የሳዑዲ ዓረቢያ መንግሥት ኢትዮጵያውያን የቤት ሠራተኞችን በገፍ ማስገባት ከጀመረ ወዲህ ነው ፡፡ ከዚያ በፊት የነበረው የስደተኞች ቁጥር 50 ሺሕ አካባቢ የነበረ ቢሆንም፣ ከ2003 ዓ.ም. ወዲህ ግን በ100 ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች እየተሰደዱ ይ ገ ኛ ሉ ።

በ2004 ዓ.ም. ብቻ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ በፈቀደው መሠረት 200 ሺሕ ሰዎች ወደ ዓረብ አገሮች ተጉዘዋል፡፡ ቀደም ሲል ሲጠቀሱ የነበሩት የስደተኛ ሠራተኞች ቁጥር በሕጋዊ መንገድ ሄደው መዝገብ ላይ የሠፈሩትን ቢሆንም ቁጥራቸው ከዚያ የማይተናነስ ወጣት ስደተኞች በሕገወጥ መንገድ ይሰደዳሉ፡፡ ይህንንም ለማጠናከር ወደ ዓረብ አገር ከሚሄዱ ዜጎች ውስጥ ከ60-70 በመቶ የሚሆኑት ሕይወታቸውን ለአደጋ ዳርገው በሕገወጥ መንገድ የሚጓዙ ናቸው፡፡ ይህ ሁሉ እየሆነ ያለው በየዓመቱ 11 በመቶ እያደገች ነው በሚባልባት አገር መሆኑ ምንኛ አስደንጋጭ ይሆን ? ልማትና እድገት ካለባት አገር ተሰዶ መቼም ሰብዓዊ መብቴን ግፈፉኝ ሆድ እቃዬን በልቱኝ ብሎ የሚነጉድ የለም።ጠግቦ ነው ካላችሁን ደግሞ ማን ጠግቦ እንደሆነ በቅርቡ መልሱን ታገኙታላችሁ።ሰላም ለኢትዮጵያ!

# ሰላም

**Tigist Belay/Pfarrkirchen**

ጥላቻን የምታቆም ብትኖር ሰላም ብቻ ናት።ሰላም ትልቅ ስፍራ አላት።ሰላም የማንኛውም ነገር መጀመሪያ ናት።ከነገሮች ሁላ የበለጠ ቦታና ድርሻ ያላት ሰላም ናት።ወያኔ ግን ዘንግቶታል።ሰላም ከሌለ ምንም ነገር ሊኖርና ሊከናወንም አይችልም።ለጦርነት ለሽብር ለሁከት ሳይሆን ለሰላም እጅ እንሰጣለን ለሰላም ተግተን ወደፊት እንላለን።ታሪክ የሚቀየረው በሰላም ብቻ ነው።ማስተዋልን ለወያኔ መንግስት አልሰጠውም እንጂ አስተውሎ አገር መምራት ሰላምን ያመጣል።

ለሰላም እንጂ ለሽብርና ለሁከት ጊዜ መስጠት የለብንም።ሰው አገር አለኝ የሚለው በአገሩ ላይ በሰላም ሲኖር ብቻ ነው።አምባገነኑ የወያኔ ስርዓት ሰላም ለምን እንደማይሻ አልገባንም።ለሰላም መናጋት ትልቁን ቦታ የያዘው የወያኔ መንግስት መቼም አይማርም።አንድ ሰው በአገሩ የመናገር የመጻፍ የመማር በግልፅ ሃሳቡን መግለፅ ካልቻለ ምኑን ዜጋ ሆነ? የወያኔ መንግስት ሁሉንም መብቶቻችንን ነፈገን።አገርን ቤተሰብን ሰላምን ነፃነትን አንድነትን ዴሞክራሲን አጣን- በወያኔ አገዛዝ።ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ ባሪያ አድርጎ ማኖሩን ያቁም።

መላው ኢትዮጵያዊ ለአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ከሚታገሉት ሃይሎች ጋር በመሰለፍ አምባገነኑን ስርዓት በማንኛውም መንገድ ከስልጣኑ ለማስወገድ ቆርጦ እንዲነሳም ጥሪዬን አቀርባለሁ። ሰላም ለኢትዮጵያ!

# የወያኔ በደሎችና ህዝባዊ መፍትሄዎቹ

**Mulugeta Gashaw/Heppenheim**

በወያኔ ስርዓት በደል ደረሰብን የማይል ካለ በዳዩ እራሱ ብቻ ነው መሆን ያለበት።በመሬት ይዞታ ኃላፊዎች በደል ደረሰብን ብለው ብዙ ሰዎች ያለቅሳሉ፡፡ በመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ ኃላፊዎች መብታችን ተገፈፈ ብለው ብዙ ኢትዮጵያዊያን አቤት ይላሉ፡፡ በወረዳ፣ በክፍለ ከተማና በአስተዳደሩ ንብረቴ ፈረሰ፣ ተነጠቅኩ፣ ታገደብኝ ብሎ የሚያነባው ብዙ ነው፡፡ ለእኔ የተሰጠ የማዕድን ቦታ ለሌላ ተሰጠ ብለው ኡኡ የሚሉ የውጭ ኢንቨስተሮችም ብዙ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ አስቸጋሪ ነው የሚል አቤቱታ በውጭ ኢንቨስተሮች እየተደመጠ ነው፡፡

በአገራችን ኢንቨስት ለማድረግ ብለን መጥተን አልተሰተናገድንም፣ ለኪሳራ ተዳረግን የሚሉ ዳያስፖራ ኢትዮጵያዊያን ብዙ ናቸው፡፡ በትራንስፎርመር ተከላ አለመካሄድ ምክንያት ፋብሪካዎች ሥራ መጀመር አልቻሉም የሚሉ ባለሀብቶች ብዙ ናቸው፡፡ በኤሌክትሪክ መቆራረጥ ማሽኖቻችን ተቃጠሉ፣ ጋዩ የሚሉ ባለሀብቶች ብዙ ናቸው፡፡ መንግሥት ውላችንን አፈረሰ ብለው የሚያዝኑ በርካታ ናቸው፡፡

ይህ ሁሉ ተደማምሮ የኢትዮጵያውያንን መንፈስና እምነት እየነካና እየጎዳ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ችግር ኢንቨስትመንትን እያደናቀፈ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ተደማምሮ ዋስትናዬና ከለላዬ ምንድነው? የሚል ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ እያስከተለ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ተደማምሮ ሥራ ላቁም፣ ወደ ውጭ ልመለስ የሚል አስተሳሰብ እያስከተለ ነው፡፡

ይሄ ባለበት ሁኔታ ስደት ቢበረክት ስህተቱ የት ላይ ነው? አብዮት ልጆቿን ትበላለች እንደተባለውና እንደበላችውም የወያኔን ስርዓት ደግፈውና ተማምነው የሚንቀሳቀሱትን ሳይቀር በምሬት የሚያሳብደው ወያኔ እንደኛ ተቃዋሚ ለሆኑትማ ምን እንደሚያደርጋቸው ማየቱ ቀላል ነው።ስለዚህ በወያኔ የሚደርሱብንን በደሎች ለማስወገድ መፍትሄው የጋራ ትግል ብቻ ነው እላለሁ።

# የወቅቱ ህዝባዊ ንቅናቄ በኢትዮጵያ

**Eden Dawit Kidane/Gießen**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የትግል እንቅስቃሴ በሙስሊሙ በክርስቲያኑ በሁሉም እምነቶችና በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ህዝቦች ሁሉ ተጠናክሮ እየታየ ነው።ህዝብ በደልና ሰቆቃው በዝቶበት እስካሁን ታግሶ ቆይቶ ነበር።ግን መታገሱና መቆየቱ በደሉን አበረታው እንጂ ሊያቀዘቅዘው አልቻለም። እናም ህዝባችን በቃኝ ብሎ ይህንን ጨካኝና አረመኔ መንግስት እና አመራር ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት በእንቅስቃሴው በርትቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።መንግስትም በበኩሉ ጠብ የመጫርና ህዝቡን ወደ ሁከት ለማስገባት አሸባሪ መንግስታዊ እንቅስቃሴውን ጀምሯል።ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ባለፈው በሙስሊሙ ማህበረሰብ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ለማሰበር አዘጋጅተዋቸው የነበሩት አውቶብሶች ምሳሌዎች ናቸው። ህዝቡ ሰላማዊ ሆኖ መንግስት አሸባሪ የሆነባት የመጀመሪያዋ አገር ለመሆን በቅታለች-ኢትዮጵያ ።ህዝባችን ከዚህ በሁዋላ የሚጠብቀው ምን ይሆን? በየቤታችን መጥተው እየጎተቱ እስኪገሉን መጠበቅ ያለብን አይመስለኝም።ትግላችን ተጀምሯልና ሁላችንም ይህን አረመኔያዊ ስርዓት ለማስወገድ መነሳት አለብን።ለዚህም ትግላችን ኢህአፓ ከጎናችን እንደሚሆን እናምናለን።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# አምስቱ የወያኔ መዘዞችና እውነታው

**Sarone Mulugeta/Würzburg**

1. ደርግን ታግለን ያሸነፍነው እኛ ነን ይላሉ ነገር ግን ደርግን ያሸነፈው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው።

2. ጠዋትና ማታ እንደፈለጉ በሚቆጣጠሩት ሚዲያቸው(ኢቴቪ ወዘተ) ስለእነርሱ ጀግንነትና ተጋድሎ ይዘፈናል። ይፎከራል፣ ጀግና ከእኛ በላይ ይላሉ በተጨባጭ ግን ለዘመናት ከጠላት ጋር ተፋልሞ ይህችን አገር ያቆየው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን አያደርግም።

3. ወታደራዊ የአመራር ቦታዎችን 100% መቆጣጠር ስለቻሉ እድሜ ልክ እንገዛለን ብለው ያስባሉ፣ ነገር ግን እሳት የሚተፋ መሳሪያ የታጠቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች ከስራቸው እንዳሉና ይህ አፈሙዝም በእነርሱ ላይ እያነጣጠረ እንዳለ አይገባቸውም።

4. ኢትዮጵያ ያለእኛ ትበታተናለች ይላሉ ነገር ግን አገርን በረቀቀ መንገድ እየበታተኑ ያሉት እነርሱ ናቸው።

5. ዘረኝነትን በአደባባይ ይቃወማሉ በተግባር ግን የዘረኝነት ጠንሳሾችና ባለቤቶች እነርሱ ናቸው።

# ወያኔና ኢትዮጵያን የማጥፋት እቅዱ

**Dagmawi Yeshtila/Treysa**

ከፍጥረታት ሁሉ የበላይና ልዩ ክብርና ቦታ ያለው የሰው ዘር መገኛ የሆነችው ውድ እናት አገራችን ኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ያላት በታሪክ ሙሁራን ዘንድ የምትወሳና በስልጣኔ ረገድም ከቀድሞዎቹ ጋር የምትሰለፍ ሃገር መሆኗ ለማንም ግልጽ ነው፡፡
ታዲያ ዛሬ ዛሬ፣ ጥንታዊ ታሪክ ሣይሆን ስለ ሀገራችን የሚዘከረው በዘር፣ በጎሣ፣ በሃይማኖት የተከፋፈለች ሃገር በመባል ምንም በገሃድ ባይጠራም በረሃብተኝነት የተፈረጀች ሀገር ከመባል አልፋ የዘረኞችና የአንባገነኖች መዲና ሆናለች፡፡ታሪክ ከጥንት ሲዘከርና ሲወርድ ሲወራረድ የመጣውን የአባቶቻችን ታሪክ አንድነቷ ተጠብቆ፣ በዘርና በጎሣ ሳይሆን አንድነቷንና ባንዲራችንን ጠብቀው ያቆዩትን የአባቶቻችን ታሪክና አጽም ከመቃብ በላይ ከፍ ብሎ ጩኸቱን እያሰማ ይገኛል፡፡

ወያኔ የስልጣን ግዜው ማብቃቱን በ1997 ምርጫ ሲረዳ ህብረተሰቡን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሣ ከመከፋፈሉም ባሻገር ሀገሪቱን በኢኮኖሚ በማድቀቅ ላይ ይገኛል። ዛሬ ፎረም በሚል የራሱን የፖለቲካ አራማጆች እንደ አሸን በማፍላት በየቀበሌውና በየመንግስት መስሪያ ቤቶች በማጎር ሠላማዊውን ህዝብ ሲያምሠው የሚመለከት ህሊና የሌለው እሱን በሠላማዊ መንገድ ሲፋለመው በታማኝ ወታደሮቹ አማካኝነት ከ9 አመት ህጻን እስከ አረጋዊያን የጥይት ራት የሆኑበት ታሪክ የቅርብ ግዜ ትዝታ እንደሆነም ቤት ይቁጠረው ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ ነውና ብሂሉ፡፡

ወገኖቼ ጥንት አባቶቻችን ሲተርቱ የቸገረው እርጉዝ ያገባል ይሉ ነበር አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የወያኔ ፎረም አባል ሆኖ ማገልገና ባርነትን መምረጥ የግድ ሆኗል፡፡ እስከ መቼ ሠው ሆነን መፈጠራችንን ረስተን እርጥባን ጠባቂ ሆነን እያጎበደድን እንኖራለን?

አሁን አሁንማ ወያኔ አገራችን ሰላም ናት ግንባታውን ተያይዘነዋል እርዱን በማለት ዲያስፖራውንና ለጋሽ ድርጅቶችን ማጭበርበሩን ተያይዞታል፡፡ የግንባታው

ብር ግን በአግባቡ እየዋለ ሣይሆን የህብረተሰቡን አሳብ እና አመለካከቱን ለመቀየር እያደረገ ያለው ስልቱ መሆኑን ተረድተን ትግላችንን አጠናክረን እንድንቀጥል ጥሪዬን አቀርባለሁ።ኢትዮጵያ በልጆቿ ለዘላለም ተከብራ ትኖራለች።

# ወያኔ እያለ ሙሰኝነትን ማጥፋትም መዋጋትም አይቻልም

**Yohanes Samson/Bad Hersfeld**

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባለፍት 21 ዓመታት ማንነቱን ከገለፀበትና የዚህ ዘረኛ ስብስብ ተክለ ሰውነት ቀዳሚ መገለጫ ከሆኑ ሁለት መለያ ባህሪያት ውስጥ አንዱ ሙሰኝነት ሲሆን ሌላው ዘረኝነት ነው።የወያኔ ስርዓት የተገነባው በሙሰኝነት ላይ የቆመውም ለሙሰኝነት ነው።

መሰንበቻውን በሙስና የተጠረጠሩ ነጋዴዎች፣ ደላሎች፣ አቀባባይ የተባሉና የመንግስት ሃላፊዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸው ከተሰማ ጀምሮ ህዝብ በስፋት እየተቸ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የተደላደለውን ሙስና ህዝብ ጠንቅቆ ከነባለቤቶቹ ያውቃል። ይረዳል። ያሸታል። ባለፈ ባገደመ ቁጥር ለድህነቱ ማስታገሻ ያላምጣቸዋል።

ሙስና ሲባል ሙስና ነው። ወንጀል ሲባል ወንጀል ነው። ህግ መተላለፍ ያስጠይቃል። አሁን እንደሚታየው ግን የጸረ ሙስናው ዘመቻ ሰፈር የለየ ይመስላል። ዋናዎቹ "ሙሰኞች" አልተነኩም። ዋናዎቹ "የማበስበሻው ባህር" ፊታውራሪዎች አሁንም እያገሱ ነው። እነዚህ አገር ወዳድ የሚመስሉ የሙስና መፈልፈያ ማሽን አምራቾች ለምን ዝም ተባሉ? የህዝብ ጥያቄ ነው? የምስኪን ዜጎች ጥያቄ ነው። በተለይም "ጠቁሙኝ እርምጃ እወስዳለሁ" በማለት ለተናገሩት አዲሱ መሪ፡፡

በኢትዮጵያ በትዕዛዝ ንብረታቸውን የተነጠቁ፣ በደል ደርሶባቸው ፍርድ እናገኛለን ብለው ወደ ህግ አምርተው በትዕዛዝ የተበየነባቸው፣ በባለጊዜዎች መመሪያ ቅርስና ርስታቸውን የተነጠቁ፣ ተራ የቀበሌ ጭቃ ቤት ሳይቀር የተዘረፉ፣ የነፍስና የወንጀል ጉዳዮች ውስጥ መዘፈቃቸው እየታወቀ ክስ የማይመሰረትባቸውና በወንጀል ተጨማልቀው አገሪቱ ላይ የነገሱ ስለመኖራቸው መነገር ከጀመረ ያው የኢህአዴግን የስልጣን ዘመን ያክል ቆይቷል።

የፌዴራሉ ዋና ኦዲተር ባልተሟላ ሰነድ 5 ቢሊዮን ብር ወጪ ሆኗል ብሎ ሪፖርት ካቀረበባቸው መስሪያ ቤቶች ውስጥ 3ነጥብ2 ቢሊዮን ብሩን ያምታታው የመከላከያ ሚኒስቴር መሆኑ ይታወቃል።ከአገሪቱ ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጀምሮ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖችም በዚሁ ችግር ውስጥ የተዘፈቁ ለመሆናቸው ደግሞ ምንም ማስረጃ ማቅረብ አያሻም።የወያኔ መንግስት ግን ይህን ተቋም ለመድፈር ተስኖት አቅም በሌላቸው ጥቂት ግለሰቦች ላይ ትኩረቱን አድርጓል።ህዝቡን ለማደናገር በጥቂት ግለሰቦች ላይ የጀመረው ስራም ግብ እንደማይደርስ የተረዳው ህዝባችን ትግሉን አጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል።ይህ የተጀመረው ህዝባዊ ትግልም ወያኔና ሁለቱን መንታ ልጆቹን ማለትም ዘረኝነትና ሙስናን ከአገራችን ምድር እስኪነቀሉ ድረስ ይቀጥላል።



# ቀን የጎደለብን ስደተኞች

**Berhanu Bayu/Schweinfurt**

እኛ ኢትዮጵያውያን በተለያየ ምክንያት ከአገራችን እንሰደዳለን ከምንሰደድባቸው ምክንያት አንዱ በአገራችን ያለው የፖለቲካ ችግር ነው።ያለብንን ችግር እያየንና ኑሮ ሮሮ እየሆነብን ቁጭ ብሎ ከመታመም እየሄዱ መሞት ይሻላል ብለን በባህር በበረሃው የምንሰደደውን ወገኖች ቤት ይቁጠረው።

በአገራችን ላይ ለዓለምአቀፍ ህዝብ ነፃነት እንዳለ ለማሳየት በተለያየ ቦታ ላይ ህዝቡ ሃሳቡን በነፃነት በሰላማዊ ሰልፍ እንዲገልፅ ቢፈቅድም በነጋታው በፎቶና በቪዲዮ የቀረፃቸውን በሰልፉ ላይ የነበሩትን ዋና ዋና ተቃዋሚዎችን ለቅሞ በማውጣት ለተለያዩ እንግልትና እስራት እየዳረጋቸው ነው።ለዚህም በዋናነት የሚጠቀሰው በደሴ በጎንደር በመቀሌና በአዲስ አበባ በተደረጉት ሰላማዊ ሰልፎች ነው።

ዛሬ ነጋዴውና የተማረው ማህበረሰብ ሃገሬ ብሎ በፍፁም በእምነት የማይነግድበትና የማይሰራበት አገር ኢትዮጵያ ብቸኛ የአለማችን አገር ናት ማለት ይቻላል።በነጋዴውና በተማረው ማህበረሰብ የህወሓት መንግስት የነጋዴዎችን ገንዘብ መዝረፍና የተማሩትን በብስጭት ከአገር እንዲወጡ ነጋዴዎችም የንግድ ቤታቸውን ዘግተው እንደ ሌላ አገር ዜጋ የተነጠቁትን ንብረት ለማስመለስ ሲለምኑ ይታያሉ።ምክንያቱም ከልጅነት እስከ አዛውንት ሜዳ ተራራውን አቋርጠው የነገዱ ወገኖች ትናንት ቤሳቤስቲ ያልነበራቸው የስርዓቱ ጥገኞች በአጭር ጊዜና በፍጥነት የናጠጡ ቱጃሮች እየሆኑ ሲመጡ ከጀርባቸው ያለው ምን እንደሆነ አመላካች ነው።

ስለዚህ መላው ህዝባችን ትግላችንን በፀረ-ወያኔ ላይ በማፋፋም እኩልነት የሰፈነባትን አገር ለመገንባት መረባረብ ይገባናል።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!


# የሙስሊሙ ህብረተሰብ ስቃይ......


**Hanan Mudi Aman/Nürnberg**

የኢህአዴግ መንግስት በእምነት ላይ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት አሁንም በሰፊው ተያይዞታል።በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ የሚደርሰው በደል ቀን በቀን ስሩን ሰዷል።የመንግስት ወታደሮች በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ በነፃነት እምነቱን እንዳያካሂድ ደንቃራ እየሆኑበት ነው።ሙስሊሙ ህብረተሰብ በጋራ በመነሳት በእምነታችን ጣልቃ አትግቡብን እምነት ፖለቲካ አስሩን ሰዷል።የመንግስት ወታደሮች በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ በነፃነት እምነቱን እንዳያካሂድ ደንቃራ እየሆኑበት ነው።ሙስሊሙ ህብረተሰብ በጋራ በመነሳት በእምነታችን ጣልቃ አትግቡብን እምነት ፖለቲካ አይደለም በማለት ተቃውሞውን ስላነሳ አሸባሪዎች እያለ እስር ቤት እየወረወራቸው ነው።በእስር ቤትም ከፍተኛ እንግልትና ስቃይ እየደረሰባቸው ነው።

የኢህአዴግ መንግስት በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ አሁንም ቢሆን መስጊድ ድረስ በመግባት ሁከት ማባባሱን ቀጥሎበታል።ያም ሆኖ ሙስሊሙ ህብረተሰብ የእምነት ነፃነቱ ቢገፈፍም ለእምነታቸው ነፃነት የሚያገርዱትን ትግል አጠናክረው ቀጥለዋል።

ሙስሊሙ ህብረተሰብ ጣልቃ አትግቡብን የራሳችንን እምነት በራሳችን አስተዳዳሪዎች እንምራ የሚለውን ጥያቄ በማንሳቱ የሚሰማው አጥቷል።የኢትዮጵያ ህዝብ አምላክ የኢትዮጵያን ሙስሊም ህዝብ ስቃይ በቃሽ ይበላት።ኢንሻአላ ቢኢዛን አላህ በቃ ይላቸዋል።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!አሜን


ዘረኝነት
ሞት
ጥፋት
ሽብር
ሰላም
betewedag
adenw


Rule of
Law
Meles
Zenawi
CUDP
Journalists
Civic groups and NGOs
Any other peaceful Opponent or Critic
Prisoners of Conscience

# አመጽ አልባ አብዮት!

**Berketi Haile/Friedberg**

በአረቡ ዓለም እንዳስተዋልነው ብሶት የወለዳቸው ህዝቦች ከጦር መሳሪያ ይልቅ መሳሪያ አልባ አብዮቶችን በማካሄድ ያቆረቆዛቸውን ስርዓት አስወግደዋል።አብዛኞቹም በኛዋ አህጉር አፍሪካ የሚገኙ በመሆናቸው የምዕራቡን ዓለም እየቀዳችሁ አህጉራችንን ልታናጓት ነው ለሚሉን አምባገነን መሪዎች ምላሽ የሰጠ የራሳችን መፍትሄ የሆነ የስርዓት ለውጥ ማድረግ ምቹ ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

በሶሪያና በሊቢያ በመደረግ ላይ ያሉት የስርዓት ለውጦች ምንም እንኳን አገሮቹን ወደ ዜሮ ድምር የወሰዳቸው ቢሆንም ጥሩ ምሳሌ ባይሆኑንም እንደኛ ባሉ ደሃ አገራት የስርዓት ለውጦቹ አውዳሚ መሆን የለባቸውም ሰላማዊና የተጠኑ ሊሆኑ ይገባል።

ስለዚህ የግብፅና የአልጄሪያን አይነት የስርዓት ለውጦች በመፍጠር ከፋፍሎ በመግዛት ላይ ያለውን የወያኔ ስርዓት ልንለውጠው ይገባል።ይህን ለማድረግ ግን ሁሉም የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባዋልና ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋፅኦ እናድርግ ጥሪዬ ነው።ሰላም ለኢትዮጵያ!

# በአንድነት የመታገያው ጊዜ አሁን ነው!

**Michael Asefa/Schweinfurt**

በኢትዮጵያ አገራችን ወደ ስልጣን የመጣው ኢህአዴግ ወያኔ መንግስት በስልጣን የቆየው በህዝብ ፍላጎት ሳይሆን በጠመንጃ አፈ-ሙዝ በታገዘ አፈና እንደሆነ የታወቀ ነው።

በአሁኑ ጊዜ የትኛው የኢትዮጵያ ዜጋ ነው ያልተገደለው ያልተዋረደው ያልታሰረው ስደትን የመረጠው በዜግነቱ ተከብሮ መኖር የሚችለው ከአምባገነኖችና ከአረመኔዎች መቼ ነው ነፃ የምንወጣው?ሰው እንዴት በገዛ መንግስቱ በአገሩ በምድሩ እየተሸበረ ይኖራል?

የወያኔ መንግስት በባህል በታሪክ በቋንቋና በደም የተሳሰረውን ህዝብ በጎሳ በሃይማኖት በዘር እየከፋፈለ እኛ ኢትዮጵያውያን ለሰላም ለፍቅርና ለአንድነት ያለንን ቃልኪዳን ለማፍረስ ሌት ተቀን እየማሰነ ይገኛል።ህዝቦች ተከባብረውና ተሳስበው እንዳይኖሩ በተወለዱበት ምድር ቤት ንብረት አፍርተው ልጅ ወልደውና አሳድገው በተከበሩበት አገራቸው ሲፈናቀሉ ይስተዋላል ለዚህም በቅርቡ ከደቡብና ከቤኒሻንጉል ክልሎች የተፈናቀሉትን የአማራ ተወላጆች ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

የወያኔ ስርዓት የኢትዮጵያን ህዝብ በቁም ቀብሯል።በተመሳሳይ በጋምቤላ ያደረሰውን የዘር ማጥፋት ወንጀል አሁንም ንፁሃን ኢትዮጵያውያን በላባቸው ያፈሩትን ንብረት በመውረስ የሚያፈናቅለውን አምባገነን ስርዓት ህሊና አለን የምንል ኢትዮጵያውያን ሁሉ ልናስቆመው ይገባል።

በእስር ከሚማቅቁት እንደነ በቀለ ገርባ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ርዕዮት ዓለሙ አንዷለም አራጌ እና ሌሎች በርካታ የፖለቲካና የህሊና እስረኞችን ከተከሰሱበት የተቀነባበረ የሃሰት ክስ ለመታደግ ሁላችንም የበኩላችንን መወጣት አለብን።

አስከፊውን የወያኔ/ኢህአዴግ ስርዓት በአንድነት ሆነን ሳንከፋፈል በስደትም በአገር ቤትም ያለን ኢትዮጵያውያን በአንድነት ለመታገል ጊዜው አሁን ነው እላለሁ።

# የሴቶች መብት ረገጣ በኢትዮጵያ

**Emy Tesfahunge/Erlangen**

በኢትዮጵያ የሚገኙ ሴቶች የመብት ረገጣ አሁንም በሰፊው እንደቀጠለ ይገኛል።ሴቶች ለመብታቸው ቢነሱም የፖለቲካ ጣልቃ በመሃከላቸው ስለሚኖር እንደሚፈልጉት መብቶቻቸውን ሊያስከብሩ አልቻሉም።

በኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለው የሴት ልጅ ወደ ትምህርት ቤት ያለመሄድ ግርዛት ያለእድሜ ጋብቻና ሁሉን አቀፍ መብት ረገጣ ነው።በኢትዮጵያ ያሉ ሴቶች ከማጀት ወጥተው ወደ ትምህርት ቤት እንዲላኩ እየተደረገ ያለው ነገር እጅግ ከሚጠበቀው በታች ነው።በገጠርም በከተማም የስርዓቱ ባለስልጣናት ሳይቀሩ ስልጣናቸውን ተጠቅመው በአስገዳጅ ያሻቸውን ሴት በመጥለፍና በማግባት በሴቶች ነጻነት ላይ አሉታዊ ሚና እየተጫወቱ ናቸው።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ሴቶች የአላቻ ጋብቻን በመሸሽም ወደተለያዩ አገሮች ባገኙት አጋጣሚ እየተሰደዱ ናቸው።ይህ ሁሉ የስርዓቱ ፖሊሲ ስህተት በመሆኑ መላው ሴቶች ክንዳችንን አስተባብረን ከአንድነት ሃይሎች ጋር በመሰለፍ የሚገባንን ድርሻ እንድንወጣም ጥሪዬን አቀርባለሁ።

# የትግሉ አስፈላጊነት

**Tigist Bantideru/Walluf**

ለነጻነት የሚደረገውን ትግል አስፈላጊ የሚያደርጉት ጉዳዮች፣

1. መሰረታዊ የመብት ጥሰት መኖሩና እኩልነት የጠፋ መሆኑ፣
2. ነባር ኃይማኖቶች እንዲጠፉና ( ኦርቶዶክስ እና እስልምና) መጤ ሃይማኖታች እንዲስፋፉ ታቅዶ የሚሰራ በመሆኑ
3. የጥቂት ጠባብ ቡድን የበላይነትን ለማንገስና ለማስቀጠል የሚደረግ እጅግ የረቀቀና መርዘኛ አካሄድ በመኖሩና ይህም የህዝብ ጥቅም እና የሃገሪቱንም ዕጣ ፈንታ ፈተና ውስጥ የሚያሥገባ በመሆኑ፣
4. በኢኮኖሚው ውስጥ የጥቂት ቡድኖች ተጠቃሚነትና የበላይነት እንዲነግስ ታቅዶ እየተሰራና እየታየም በመሆኑ
5. የአንድን ጠባብ ቡድን የስልጣን ዕድሜ ለማራዘም ታቅዶ የሚሰራ በመሆኑ
6. ይህንን በአባቶቻችን መስዋትዕነት የኖረ ሃገር ለተተኪው ትውል የማስረከብ ግዴታ ስላለብን
7. ጥቂቶች ሲቆጠሩ ጥቂት መሆናቸው ስለማይቀርና መሸነፋቸውም የግድ ስለሆነ ትግሉን በስርዓት መምራት ያስፈልጋል፡፡

# የድርሻችንን እንወጣ

**Doriyan Kassahun Fanta/Hof**

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ቀላል የማይባል ግፍ እና በደል ሲፈፅም ለ22 ዓመታት ዘልቋል።ታዲያ እነዚህ ግለሰቦች በፈፀሙት ግፍ ብዙ ህፃናት ያለ ወላጅ ቀርተዋል፣ብዙ አዛውንት ያለ ጧሪ ቀርተዋል፤አብዛኛው ህዝብ በአምባገነንነት አገዛዝ የበለጠ ጨካኝና ለህዝብ የማይራራ የጥቅምና የአረመኔ መንግስት ነው።የወያኔ መንግስት ማለት የህዝብን ችግር መራብ እንዲሁም ስቃይ የማይረዳ ህዝብን በአቅሙ ያፈራውን ንብረት እየቀማ የገበሬውን መሬት ንብረት በመንጠቅ ለግል ጥቅማቸው የሚያሳድዱት ለኢህአዴግ አባሎች እየሰጠ ምስኪኑን የኢትዮጵያ ህዝብን እንዲቆረቁዝ እያደረገ ቆይቶ በማድረግ ላይም ነው።

ስለዚህ ሁላችንም ይህንን ስርዓት ከስሩ ገርስሠን ለመጣል ነፃነትና መብት ለማስከበር ከሚታገሉ ወገኖች ጋር በመተባበር ፍትህን፣ነፃነትን፣እና እኩልነት የሰፈነባት ሀገር ለመገንባት መነሳሳት ይጠበቅብናል።

# የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት መቼ ይሆን?

**Fissha Tsion Hailegeberile/ Kronach**

የተከበራችሁ ውድ አንባቢያን እንደምናውቀው የዘረኛው መንግስት ሀገራችንን ማስተዳደር ከጀመረ አንስቶ እስከአሁኑ ጊዜ ነፃነታችንን ገድቦ መብታችንን አፍኖ ሀገራችንን ጨቁኖ ብሔር ብሔረሰቦችን ከፋፍሎ ዘመን ዘመንን እየወለደ ከዚህ ደርሰናል።

ስለዚህም ወያኔ ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድም ጊዜ የነፃ መብት ሰጥቶ አያውቅም እና ለዛሬ ርዕሴ ነፃነት የሚለውን መረጥሁ።ሀገራችን ኢትዮጵያ በፌደራሊዝም ሥርዓት እንደምትተዳደረው ሁሉ የነፃነት መብት ግን ታስቦም ተነግሮም አያውቅም።ለምሳሌ በነፃነት የመናገር መብት በነፃነት የመፃፍ መብት፣በነፃነት ፖለቲካን የማራመድ መብት፣በነፃነት ነግዶ እና አትርፎ መኖር፣በነፃነት ሀገሪቷ ውስጥ ኢንቨስትመንት ማካሔድ መብት ሀገራችን ውስጥ እኔ እንደማውቀው በፊደላት የተፃፉ ቃላት እንጂ የሚተገበሩ ቃላቶች አይደሉም።ለምን ብንል የገዢው መንግስት የወያኔ ፓርላማ ብዙ ነገሮች ጊዜውን ሰአቱን ገድሎ ሲወያይ ይታያል።መተግበሩ ግን ራስን እንደማጥፋት አድርጎ ይቆጥረዋል።ምክንያቱም ለሀገሪቱ ህዝብ ነፃነቱ የሚነገረው በወሬ ብቻ ነው።በተግባር ግን የምናየው ወደ ወህኒ ማውረድ ብቻ ነው የወያኒ መንግስት ትልቁ የተግባር ድርሻው በነፃነት የሚናገሩትን ወይም በተግባር የሚሰሩትን እየለቀመ ወደ እስር ቤቶች እና ወደ ወህኒ ቤቶች ማውረድ ነው።ምክንያቱም ነፃነት የሚባለው ቫይረስ ለወያኔ ትልቁ ጠላት ነው።

ውድ አንባብያን የኢትዮጵያውያን ልጆች የሚያውቁት እውነታ አለ እርሱም ወያኔ ዕድሜውን ለማራዘም የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች የተለያዩ ናቸው።አንድ ምሳሌ እናንሳ ምርጫ በመጣ ቁጥር በሀገራችን ውስጥ የሚወጡ ነፃነቶች በቁጥር እጅግ ብዙ ናቸው ፓርላማውም ብዙ ነገሮችን ይናገራል ብዙ ነገሮችን ያፀድቃል።ለምን ለምርጫ መቀስቀሻ ለአንድ አመትም ሆነ ለሁለት አመት ይጠቀምባቸዋል።ምርጫውን በውሸት ሲያሸንፍ ግን ምን ብሎ መግለጫ ያወጣል።የማሻሻያ መብቶች ብሎ መብቶችን በሙሉ ያግዳቸዋል።የመናገሩም የመፃፉም የመነገዱም ሁሉም ተመልሰው ይዳፈናሉ።ምክንያቱም ወያኔ በራሱ እና እርስ በራሱም አይተማመንምና።ወገኔ ነፃነታችን አሁን ነው ለወገናችንም ለራሳችንም ነፃነት አብረን እንታገል።አበቃሁ።

# በቃ

**Yared Tadese Abraham/Hof**

በወያኔ የሃያ ሁለት አመታት አገዛዝ በቀጠለው የጅምላ እስርና እንግልት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሰዶ ማሳደዱ ቀጥሎ በሺዎች የሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎቻችን ማዕላዊ ተብሎ በሚታወቀው የምርመራና የስቃይ ስፍራ አሳራቸውን እያዩ ሲሆን የአንድ ሀገር ዴሞክራሲያዊነት መለኪዎች ከሆኑት ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ውጪ ለእስርና ለእንግልት እንደሚዳርግ የአደባባይ ምስጢር ነው።ወያኔ በተደጋጋሚ በዘመቻ መልክ ባልተረጋገጡ ወይም ሊረጋገጡ በማይችሉ አሉባልታዎች በርካቶችን ከማሠሩም እንዲጡ እየፈረደባቸው ይገኛል።ሥርዓቱ መገልገያ መሣሪያ እያደረገ ያለው የፀረ-ሽብር ህግ ተብሎ የሚታወቀውን የህግ አንቀጽ ሲሆን ይህ ሰፊና አደናጋሪ ትርጉሞቹን የያዘ አንቀጽ ሰላማዊ ተቃውሞን ከማፈኑም ባሻገር ለፖሊስ ኃይሉ የብርበራ፣የአሰሳና የማሰር ከፍተኛ ስልጣንን ሰጥቶታል።

በመሆኑም ዜጎች የተጫነብንን አፋኝ አገዛዝ ለማስወገድ እንዲሁም የህሊናና የፖለቲካ እስረኞችን ነፃ ለማውጣት በጋራ እንነሣ።

# በአንድነት እንታገል

**Metasebia Keflu Teshome/Kronach**

የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት ልዕልናውን አስከብሮ መቆየቱ የሚታወቅ ነው።ይህንንም ማድረግ የቻለው በአንድነት ፀንቶ በመቆሙ ነው። ተቻችሎና ተከባብሮ በመኖሩም የሀገሩን ዳር ድንበር አስጠብቆ ለትውልድ ሲያሸጋግር ኖሯል።ስለሆነም ተቻችሎና ተስማምቶ መኖር ሀገርን ተከብራ በነፃነት እንድትኖር ብቻ ሳይሆን በልማትና በዕድገት ጎዳና ለመገስገስም አይነተኛ መፍትሄ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነቱን ጠብቆ በመኖሩ ታላቅ ታሪክ የሰራ ቢሆንም ዛሬ ወያኔ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ ግን ፍትሃዊና ነፃ አስተዳደር የውስጥ ሰላምና መረጋጋት አግኝተን አናውቅም።ይህ አምባገነናዊ ሥርዓት በህዝቡ ላይ በሃይል የተጫነ ቀምበር ስለሆነ ልማት፣ዕድገት፣ሠላም፣ሃሳብን በነፃነት መግለፅ፣በነፃነት መደራጀት እንዲሁም ተመጣጣኝ የምጣኔ ሀብት ክፍፍል ማጣት በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ ህልውና አደጋ ላይ ጥሎታል።

የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በርሱ በጥርጣሬ እየተያየ እንዲኖር ዘረኛ ፖሊሲ ዘርግቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ስለዚህ እርስ በርስ ተስማምተንና ልዩነቶቻችንን አቻችለን በጋራ አላማና በብሔራዊ አጀንዳ ዙሪያ ተሰባስበን የወያኔን ሥርዓት በአንድነት ታግለን ማስወገድ አለብን።

# ለለውጥ እንታገል

**Gizachew Dametew Fikre/HOF**

የኢትዮጵያ ህዝብ ልማትን ብቻ ሳይሆን የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበሩ በማለት ለዘመናት ተጋድሎ ማድረጉንና የተለያዩ ተፅዕኖዎች መፍጠሩም ይታወቃል።ላለፉት ሥርዓቶች ከስልጣን መገርሰስም ዋነኛ ሚናውን የተጫወተው ይኸው ህዝባችን ነው።በተለያዩ ጊዜያት በህዝብ አመፅ እና ትግል ስር ተደብቀው ስልጣንን የሚጨብጡ ሹማምንት ከሀገራዊ ጥቅም ይልቅ ለሆዳቸው እያደሩ ኢትዮጵያን ከማሳደግ ይልቅ ወደኋላ እየጎተቷት ይገኛሉ።ወያኔም ለኢትዮጵያ ወቅታዊ ችግሮች በዋናነት ተጠያቂ ነው።

የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲሁም የምግብ ዋስትናን በሀገራችን ለማረጋገጥ ወያኔ አቅሙም ፍላጎቱም የለውም።

የተለያዩ ሀገራት በቢሊየን የሚቆጠር የገንዘብ እርዳታ ቢያደርጉም ይህ ነው የሚባል ስር ነቀል መሠረታዊ መሻሻል መታየት አልቻለም።በፖለቲካውም በኩል በተቃዋሚ ጎራ መሰለፍ እንደአሸባሪ በመቆጠሩ በርካቶች ዕጣ ፈንታቸው በእስር መማቀቅ ሆኗል።

በመሆኑም ለህዝባችንና ለሀገራችን ዕድገት ደንቃ ቢስ የሆነውን የወያኔ መንግስት ለማስወገድ በአንድነትና በሀገራዊ ስሜት ልንተባበርና ማናቸውምን የትግል ስልቶች ልንጠቀም ይገባል።

# አባይን ለፖለቲካ መሣሪያነት መጠቀም ይቁም

**Yohannes Selamu Benti/Hof**

በሀገር ውስጥ ያልተመለሱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥያቄዎች ወያኔን ሲያስጨንቁት ጉዳዩን ለማዳፈን የአባይን ጉዳይ በሰፊው ማራገቡን ቀጥሎበታል።
የነፃ ፕሬስ፣የሰብዓዊ መብት ጥበቃ፣ የመድብለ ፓርቲ ምስረታ፣ የዜጎች እኩልነትና የመደራጀት መብት ጥያቄዎች አላነቃንቅ ያሉት የወያኔ መንግስት እነዚህን መመለስ ሲሳነው አባይን አቅጣጫ ማስቀየሪያ መሣሪያ አድርጎታል።

የአባይ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ የወያኔ መንግስት መቼም ቢሆን ስልጣኑ አካባቢ የሚነሳበትን በሰላማዊ ትግልም ቢሆን ማየት አይፈልግም።በሀገር ውስጥ ወያኔ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አረጋገጠ ማለት ዜጎች የፖሊሲውን ከፋፋይነት ስለሚያውቁ ወዲያውኑ ከስልጣኑ ያስወግዱታል።በመሆኑም ህዝባዊ ጥያቄዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ጉዳዩን ውጫዊ እያደረገው ይገኛል።የሀገር ውስጥ ችግሮች እስካልተፈቱ ውጫዊ ጉዳዮች የታሰበላቸውን ግብ ይመታሉ ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው።የሀገራችን ህዝብም በወያኔ የተለያዩ ማደናገሪያዎች ሊታለልና ለወያኔ ተጨማሪ ዕድሜን ሊሰጠው አይገባም።

ስለዚህ በአባይ ስም ሀገራዊ የውስጥ ችግሮችን ለማዳፈን የሚጥረውን የወያኔ መንግስት በተባበረ ክንዳችን ልናስወግደው ይገባል። ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

# መፍትሔው እኛው ነን

**Atnaseiy Tesfaye Wegayehu/ Nürnberg**

ላለፉት 22 አመታት ስልጣኑን የተቆጣጠረው የወያኔ መንግስት ለኢትዮጵያ ህዝብ የፈየደው ነገር ቢኖር ድርቅ፣ስደት፣እስር፣ኢ-ሰብዓዊ አገዛዝና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ነው።በወያኔ የአገዛዝ ዘመን የሀገሪቱ ዕድገት የቁልቁለት ጉዞ ሲሆን ለአብዛኛው ህዝብ ያተረፈው ነገር የለም። አምባገነኑ የወያኔ መንግስትም በተጭበረበረ ምርጫ እና በአፈሙዝ አገዛዙን አጠናክሮ ህዝባችንን አሳር ፍዳውን እያሳየው ይገኛው። ነገር ግን ይህን አፋኝ የወያኔ ሥርዓት የውጭ ኃይሎች ታግለው ከሥልጣን እንዲያስወግዱልን መጠበቅ የለብንም።

የወያኔ መንግስትን ግብዓተ መሬት ለማፋጠን ደግሞ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም ከእያንዳንዱ ሀገር ወዳድ ዜጋ ይጠበቃል።በመጀመሪያ የወያኔን ህገ-ወጥ ተግባር ለመከላከል ምን እርምጃ እንውሰድ?ከኛስ ምን ይጠበቃል? በሚለው ላይ ልዩነታችንን በማስወገድ የጋራ መግባባት ላይ ልንደርስ ይገባል።

በተለይ በተቃዋሚው ጎራ በምንገኘው ወገኖች መሃል አንድነትን በመፍጠር የጋራ ጠላታችን የሆነውን የወያኔን መንግስት ከከፋፋይ አገዛዙ ለማስወገድ ክንዳችንን ልናበረታ ይገባል።እኛ በውስጣችን ሰላምና መተጋገዝ እንዳይኖር ወያኔ የሸረበውን ሴራ በማክሸፍ ስልጣኑን እንዳያራዝም በአጭሩ ልንቀጨው ይገባል።

# የመሬት ቅርምቱ አደጋ

**Simret Ayalew Mengescha/ Höckstadt**

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት የሀገሪቱን ምሁራን እያሰረና እያሰቃየ፣ህዝቡን እየዘረፈና እየገረፈ የሚያደርሰው በደል ሳያንሰው በኢንቨስትመንት ስም የኢትዮጵያን ገበሬ መሬቱን በመንጠቅ ለባዕዳን በመሸጥ ላይ ሲሆን እነዚህ ባዕዳን በኢትዮጵያ ምድር ላይ ያመረቱትን ምርት ወደየሀገሮቻቸውና ወደሌላው የውጭ ምንዛሪ ወደሚያጋብሱበት ሀገር ኤክስፖርት ሲያደርጉ በገዛ ሀገሩ ምርጫ ያጣው የሀገራችን ገበሬ በቀን ሠራተኝነት እንዲቀጠርና በዘመናዊ ባርነት ሥር እንዲወድቅ ተደርጓል።በእርግጥ የውጭ ኢንቨስትመንት በየትኛውም ሀገር የተለመደ ቢሆንም አሁን በሀገራችን እየታየ ያለው አይነት የሀገሬውን ህዝብ በችግር ለማሰቃየትና በባርነት ሥር ለመጣል የሚደረግ ጉዞ ኢንቨስትመንት ሳይሆን ዘመናዊ የቅኝ አገዛዝ ስልት መሆኑን ከወዲሁ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ይህ ዛሬ በግብርና ክፍለ-ኢኮኖሚው ላይ የተጀመረው መረን የለቀቀ አሰራር የኢትዮጵያ ህዝብ በረሃብ እንዲቀጣ የከተማው ነዋሪ በቂ ምርት አግኝቶ ስለማይገዛ ከገቢው በላይ የእህል ዋጋ እንዲንር ዘራፊዎችና የጊዜው የሥርዓቱ አባላትና ደጋፊዎች ተንደላቀው እንዲኖሩ ሲያደርግ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ ለረሃብ አደጋ ያጋልጠዋል።

በጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን ላይ የደረሰውን ስቃይ በማስታወስ መጪው ትውልድ ውስብስብ ችግር ውስጥ ከመውደቁ በፊት ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህንን ፋሺስታዊ መንግስት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በህብረት መታገልና አሽቀንጥሮ መጣል ይኖርበታል።

# በፅናት እንታገል

**Addisalem Tegne Abera/Kronach**

የጭቁን አገዛዝ ሥርዓት በሰፈነባት ሀገር ህዝብ ከድህነትና ከድንቁርና ልገላገል፣ሰብዓዊና የሲቪል መብቶቼና ነፃነቶቼ ይከበሩልኝ የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ ሥርዓቱ አይፈቅድም።ህዝብ በራሱ ስሜትና ፍላጎት ተነሳስቶ የመብት ጥያቄዎች ካነሣ የአገዛዙ ምላሽ ስልጣን ላይ ያወጣውንና ስልጣን ላይ መቀጠል ያስቻለውን ከፍተኛ የጉልበት ኃይል በመጠቀም ማፈን ብቻ ነው።የእኛ ፍላጎት የኢትዮጵያን ህዝብ ከፋፍሎ ለመግዛት ሲባል የዘር ልዩነታችንን ምክንያት በማድረግ በስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ የሚያስራጨውን መርዘኛና አደገኛ የዘረኝነት መርዝን ከሕብረተሰባችን ውስጥ በጊዜው ለመንቀል ነው።

የመንግስት ስልጣን ላይ መቀመጥ ትርጉሙ ለህዝብ ምንድነው? ብሔርና ብሔረሰብን በማጣላት፣ሠላምን በመንፈግ ሁሉም የጎሪጥ እየተያየና እየተፈራራ እንዲኖር ማድረግ ነውን?አይደለም!ጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! ጨካኝና ርህራሄ የሌለው ይህ መንግስት አንዱን ሲያስር ሌላውን ሲገድል ያለ አዕምሮ እንደሚመራ እንስሳ ፍፁም ርህራሄ እንደሌለው ይታወቃል።

ስለዚህ ትግላችን ከፊታችን የተረጋገጠውን ከባድ ፈተና ለማለፍ መሆኑን መረዳት አይሳነንም።ይህም ሆኖ በሰው ልጆች የጋራ ጥረት የማይቃለል ምንም አይነት የጋራ ችግር የለም በሚለው የአብሮነት ራዕይ መሠረት ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈን በጽናት በመታገል በጋራ ወዳለምነው ግብ እንደምንደርስ በፅናት ማመን ይገባናል።

**We are the voice of the voiceless ! RESPECT Press Freedom in Ethiopia!!!**

# ኮፈሌ በደም ታጠበች

**Wube Alemayehu/Münnerstadt**

ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ኮፈሌ ከተማ የመንግስት ታጣቂ ሀይሎች በንፁሃን ዜጎች ላይ የተኩስ እሩምታ ሲያወርዱ ውለዋል።ድራማውን እንዲቀርፁ የተላኩት ግለሰቦች የሚንቀጠቀጥና በወቅቱ የተፈጠረውን አለመረጋጋት በሚወዛወዝ የቪዲዮ ተንቀሳቃሽ ምስል ለማሳየት ሞክረዋል ።ከተንቀሳቃሽ ምስሉ ጀርባ ምንም ገላጭ ድምፅ ባንሰማ ምናልባትም ክስተቱ በአንዱ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት አልያም ደግሞ በጎረቤታችን ሶማሊያ የተፈፀመ ይመስለን ነበር።የመንግስት የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ቤት (etv) በሪፖርቱ የሟቾች ቁጥር ሶስት መሆናቸውን ገልፆ ለሟቾቹ ተጠያቂዎች አከራሪዎች ናቸው ብሏል።

በምን አይነት ስሌት ግን እነኚህ ሁሉ ሰላማዊ የተቃውሞው ተሳታፊዎች አክራሪዎች እየተባሉ እንደሆነ መንግስት ምንም ምላሽ ለመስጠት አልፈለገም።መንግስት ተቃዋሚዎቹ ሰላማዊ መሆናቸውን እያየ አላየም እየሰማም ጆሮው ተደፍኗል። ኢሳት በበኩሉ የመንግስት ታጣቂ አይሎች በንፁሀን ላይ በወሰዱት ሀይል የተሞላበት እርምጃ የማቾቹ ቁጥር ከአስር በላይ መድረሱን ሪፖርት አድርጓል።

cnn i Report መንግስት በሀያማኖታችን ጣልቃ ገብቶብናል ብለው ተቃውሞ በወጡ ሰላማዊ ተቃዋሚዎችና በመንግስት የፀጥታ ሀይሎች መካከል በተፈጠረ ግጭት 25 ግለሰቦች መገደላቸውን ዘግቧል።በኮፈሌ ከተማ በንፁሃን ዜጎች ላይ የተፈፀመውን ግድያ ስመለከት ይህ መንግስት ወደየት እያመራ እንደሆነ አንድ መልዕክት አስተላልፎልኛል።መልዕክቱም ይህ መንግስት የሀገሪቱ የሉአላዊነት ጠላት መሆኑን ነው።

የዚህ መንግስት የመጨረሻ ፍላጎትና ግብ በህዝቦች መካከል ትርምስና መጠላላትን በመፍጠር የሀገሪቱን ሉአላዊነት ማሳጣት እንደሆነ ግልፅ ነው።በእርግጥ በድርጊትም ሆነ በአስተሳሰብ ከዚህ በላይ ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጭና የህዝቦች ሉአላዊነትን የሚደፍር ማሳያ መጠበቅ አያስፈልገንም።ሙስሊሙ ማህበረሰብ ሙብቱን በሰላማዊና በሰለጠነ መንገድ ነው እየገለፀና እየጠየቀ ያለው።ሰላማዊ ተቃውሞን ቁጭ በማለትና እጆችን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎ በማንሳት ብቻ ተቃውሞን መግለፅ እንደሚቻል ሙስሊሙ ማህበረሰባችን እያሳየን ነው።

መንግስት አሁን በያዘው የፅንፈኝነት አቋሙ ከቀጠለ ሀገሪቱ ወዳልተፈለገ ብጥብጥ ልታመራ የምትችልበተ አጋጣሚ አይቀርም።መንግስት ለዚህ መሰረት የሚሆን የጥላቻ አስተሳሰቦችን ማምረት ከጀመረ ሁለት ዓመታት ሊሞላው ነው። የዚህ የአስተሳሰብ ክፍፍልና የሚፈጠረው የጥላቻ መንፈስ የመታጠቢያው ጊዜ ቀላል መስዋእትነት የሚጠይቅ አይሆንም።

# ኢትዮጵያን እናድን!

**Hanna Kebede/Würzburg**

የወያኔ መንግስት ራሱ ላወጣው ህገ መንግስት እንኳን መገዛት የማይችል ስርዓት አልበኛ ወደ መሆን ደርሷል።ከአምስት ሺ ዓመታት በላይ ታሪክ ያላትን ኢትዮጵያን ለማጥፋት አልሞም በመስራት ላይ ይገኛል።በዘርና በጎሳ የተከፋፈለች አገር ለማድረግም የጠነሰሰው ሴራ መዘዝ ማስከተል ጀምሯል።

ህወሓት/ኢህአዴግ በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ የሆነ ሽብርን በመፍጠርም እራሱን ከአገራዊ ወንበዴነት ወደ አህጉራዊ አሸባሪነት ደረጃ በማሳደግ ለጥቂት ስግብግብ ቱጃሮች ቅጥረኛ በመሆን ዳግም ህዝቦችን ወደ ቅኝ ግዛትነት እንዲገቡ ያለመና መንገድ እየጠረገ መሆኑን በአሁኑ ሰዓት በአገራችን የሚካሄደውን የመሬት ወረራ በማስረጃነት ማየት በቂ ነው።

ስለዚህ በሁሉም ዘርፍ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የነፃነት ትግል በአገራችን ውስጥ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀልናየዘር መድሎ ስርዓትን ብቻ ሳይሆን ቀጥሎ በአፍሪካ ዳግም ሊመጣ የሚችለውን የቅኝ ግዛት ማንሰራራት በእንጭጩ ማስቀረት ጭምርም ስለሆነ የኢትዮጵያ ጎረቤት አገሮች ለዚሁ ትብብር እንዲያደርጉ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን መረባረብና የኢትዮጵያን መጻኢ እድል ብሩህ የማድረግ ሃላፊነት እንዳለባቸው በመገንዘብ ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋፅኦ ማድረግ አለብን እላለሁ። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

# ታሪካችንን ማደስ ይጠበቅብናል

**Mulugata Mersa Yimer/Würzburg**

በአሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ሰው መኖር የማይችልባት ሃገር እየሆነችነው። ምክንያቱም ብዙዎች ያለምክንያት በጭከና ሞተውባታል፣ተደብድበውባታል፣ታስረውባታል፣ሃገር ጥለው እንዲሰደዱ ግፍ ተፈጽሞባቸዋል። የተወሰኑ ባለስልጣናትና ጥቅመኞች ደግሞ ተደስተውባታል።እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞችም በፈጠራ ወንጀል ክስ በቅርቡ ተመስርቶባቸው በእስር ላይ ይገኛሉ።የሚገርመውና የሚያሳዝነው ነገር የተከሰሱት በአሸባሪነት መሆኑ ነው። በኢትዮጵያ አሸባሪዎችና ወንጀለኞች ባለስልጣኖች ሆነው እያለ በንፁሃን ዜጎች ላይ እንዲህ አይነት ስም መስጠት እየተለመደ መጥቷል።

ላለፉት ሃያ አመታት በእስር ቤት ወድቀው በስቃይና በመከራ ውስጥ ያሉት የፖለቲካ እስረኞችም እንዲሁ ተመሳሳይ ናቸው።የነዚህ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጆች የከፈሉትና በመክፈል ላይ ያሉት መስዋትነት በዋጋ የማይለካ እኛን እንቅልፍ የማያስተኛ፣ ለነፃነትና ለፍትህ መንገድ የሚያሳይ በመሆኑ በተግባር ልንሳተፍበትና የታፈነውን ድምፃችንን ለአለም ህብረተሰብ ልናሰማ ይገባል። የነፃነት አምላክ እግዚአብሔር ያለገደብ የሰጠንን ነፃነትና መብት የወያኔ መንግስት በጉልበትና በትምክህት ሊነጥቀን አይገባውም። የቀደሙ አባቶቻችንን ወኔ ይዘን የተዘረፍነውን ነፃነት ከወያኔ መንጋጋ መንጭቀን በመመለስ ታሪካችንን ማደስ ይጠበቅብናል።

# ለአንድ አላማ በጋራ እንቁም

**Asnakch Telahun/Würzburg**

እንደሚታወቀው በሃገራችን ኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው ግፍና ጭቆና ከቀን ወደ ቀን ስር እየሰደደ መጥቷል፡፡ ምክንያቱም ገዢው የወያኔ መንግስት ሃገሪቷን መምራት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷልና፡፡እንዴት ቢባል ገዢው ፓርቲ በስልጣን ዘመኑ ሃገራችንን ብዙ ነገሮች አሳጥቷል፡፡ ለመጥቀስ ያህል እድገቷ ኋላ ቀር ሆኗል፣ በብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል የነበረው መከባበርና መፋቀር ደብዝዞ በምትኩ ጥላቻና መናናቅ ሰፍኗል፣ የሰው ልጅ እንደዜጋ ማግኘት የሚገባውን መብት ተነፍጎ ያለነፃነት በስጋት ኑሮውን ይገፋል፣ የህግ የበላይነት ተረስቶ ማንኛውም የገዢው ፓርቲ አባል የሆነና ትንሽ ስልጣን ያለው ሰው ተነስቶ የፈለገውን ማድረግ መብቱነው፡፡ ይህ እንዲሆን ያደረገው የወያኔ መንግስት የፈጠረው ክፍተት ነው።የህግ የበላይነት የሚባል ነገር የለም፣ ተጠያቂ ሊያደርገው የሚችል አካል ስለሌለ የሚፈልገውን ማድረግ መብቱ ነው፡፡የሚናገር ወይም የሚቃወም ካለ ይታሰራል። ታዲያ ወገኖቻችን እንደዜጋ ማግኘት የሚገባቸውን የመናገር፣ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ እና የመሰብሰብ ወዘተ.. መብታቸውን ሊያገኙ የሚችሉት መቼ ነው? ከዚህስ የአፈና አገዛዝ ነጻ የሚወጡት መቼ ነው? ግፍና ጭቆና ይብቃ! የወያኔ መንግስት ሊወርድ ይገባዋል! ህዝባችን ክንደ ጠንካራና ወኔው የሚያኮራ ነው።ስለሆነም ሁሉም በአንድነት ለአንድ አላማ በመቆም ነፃነቱን ሊያስመልስ ይገባል።

**የጥላ መጽሔት አዲሱ አድራሻ**

**Mesfin Abraha**
**An der obergeis 1**
**36251 Bad Hersefeld**


2013
EID
MUBARAK


May the choicest blessings of Allah
fill your life with peace ,
joy and prosperity !
EID
MUBARAK !

# Water politics in the Nile Basin

**Debebe Kebede/Goch**

The Nile River is subject to political interactions for centuries. The water course of this river, consideres to be the longest in the world with the total length of 6,650 km, crosses 11 states whose combined populations constitute 40%of the entire population of Africa (Tesfaye, 2001). The Nile has two major tributaries, the White Nile and Blue Nile.the source of the blue nile ,which constitutes 86%of the volume of the nile,is Ethiopia and to some degree Eritrea,while the contribution of the white nile is shared amongst Tanzania, Rwanda, Brundi, Kenya, Uganda, southern sudan and the democratic republic of congo (Ashok,1997). The two lower riparian states,Egypt and Sudan, are traversed by the nile that joins in Khartoum. The states through which the nile passes need the water primarily for irrigation and, in varying degrees,for hydroelectric power generation,domestic use ,transportation, industrial consumption(Abiodun,2001).

The nile basin is characterized by high population growth,poverty,food insecurity,environmental degradation , water scarcity,and on top of it all,the potential for conflict over water(Niveen,1997).the demand for fresh water in nile basin riparian states is likely to rise while the supply will decrease in the future (Russel,1999).As the population of the nile basin continues to expand,water scarcity will be at the fore front of the region`s problems(Henrike,2003).Despite the enormous potential of the nile ,massive poverty and food insecurity have been an enduring future of the nile basin.

Given the scenarios discussed above, Ethiopia has started the actual of the great Ethiopian renaissance dam(GERD)in 2011. This has brought a fresh political conflict especially between Ethiopia and Egypt. But many people believe that the two countries used the issue to divert the attention of their respective people from internal political affairs. In this regard, most Ethiopians believe that the government of Ethiopia is using the construction of the dam as a strategy to prolong its dictatorial regime.
As an individual,I strongly believe that Ethiopians are looking for a regime change before anything else to end up human right violations,corruption,nepotism and other political and social chaoses. So that,it is time for all opposition political parties to mobilize and aware the general public how to dismantle the dictatorial regime in Ethiopia with non violent mass action.

# Amharas Suffered Again

**Habtam Alemneh Belay/ Heusenstamm**

When is going to be the end for the suffering of Amara people? Like Dictator Meles, PM Haile Mariam is going to have Amara blood in his hands. He should realize that revenge seems miles away but it will come for sure. The saying goes as "Shewa Sigezegez Enji, Sitl Aytawekim".that means ``Shewa can start to attack, but can not go up to the end`` but now the say is already changed. These days, all Amharas are out to teach Woyanes a lesson. Yes, what goes around will come around. Time will show us. Anyhow, we will fight in all ways until the following are achieved:

1) Freedom to the Amhara people to move around throughout the lands of their ancestors.
2) Justice to those genocide victims in Bedeno and Arba Gugu by Woyane and Oromo fanatics.
3) Justice to those who were deported from Gura Ferda by The dictator Ex-Southern state governer Shiferaw Shigute and Co.
4) Justice to those forcefully moved from Benishiangul by EPRDF dicatators Haile Mariam Desalegn, Ahmed Nasir, and Sebhat Nega.Freedom Freedom Freedom!!!

# Egypt`s Situation: a good lesson for Ethiopians

**Bisrat Girir/Bisrat Weldemikael-Aßlar**

We oppositions won the election in 2005 and tplf juntas took made the coup and put People elected opposition party leaders in prison for life. They could have killed them but they knew the consquences.

So as long as Woyane hold the military as a monopoly, the masacre is unavoidable if and when the non-EPRDF`s take Power. The Egyptians military junta thought they are dictators they are not made up of one ethnic Group

and hated by all where as EPRDF enjoys the vice- versa from top to bottom.

So for their own survival they have to massacar to silent the majority. that is why:- we oppose strongly that only EPRDF members hold Power in the military. I dont think when is the right time for Woyanes to understand this?

We know what happened to derg and all Ethiopians. And it is my duty to tell TPLF that their policy is a devastating one.they will gonna face the charges that they deserve like the Mengistu regime officials soon! Let`s unite and struggle for our freedom and equality!

# Justice for Oromo people!

**Habtamu Tesfaye/Fulda**

Woyane has increased his violence in oromiya many folds over. Today, more Oromo people killed than any time before; a lot also arrested.

The woyane regime evicting the Oromo people from their land without any compensation and sells the land for foreign investors like India and different Arab countries.

Oromo skilled man power, the one whom struggle for justice, democracy, and human rights are suffering and terrorizing by the government. These problems are the cause for the people to left their homeland.

The regime has not stopped its harassment on the Oromo students of all universities.they all are subject to torture and death. Many of them left their countries and obliged to live in Arab lands like slaves. They face a lot of problems such as tortured, chemicalized, isolated, and sexual harassment by their employers.

So, we are responsible to alleviate the suffering of our brothers and sisters. We have the responsibility to protect our country.

Therefore, we people of Oromo can have our freedom by avoiding the dictatorial regime with the help of Oromo Libration Front (OLF). Victory to the people of Oromo!

# No Human Right in Ethiopia

**Hilina Dawit/Nürnberg**

Last month ,Members of a European Parliament human rights delegation have been blocked from visiting an Ethiopian prison, and are concerned about the human rights situation in that nation.

The European Parliament Subcommittee for Human Rights wrapped up a visit to Ethiopia to assess the country's human rights situation. The delegation had a trip scheduled to the infamous Kality prison just outside the capital, Addis Ababa. The facility is known for housing political prisoners in harsh living conditions.

In spite of previous assurances from Ethiopia's government, however, the group was denied access to the prison.

“We were more than disappointed. Personally I cannot understand the reasons behind it," said Protasiewicz a delegate from European Union. "Because if you don't want to show the parliamentarians how people are detained and the conditions in the prisons, it is clearly that something is to be hidden.” She added.

This shows us a clear danger of Human right in Ethiopia. Because of their attitudinal difference with Woyane regime, People are starving, harassing, and torturing in all prisons of Ethiopia. So, EU members should have to use their powers to stop the bad treatment or **Torture** of Ethiopian regime on its own people. And I urge all Ethiopians to unite and struggle to avoid the inhuman regime from our country. Ethiopia will prevail!




**We are the voice of the voiceless ! RESPECT Press Freedom in Ethiopia!!!**

# ጉድባ መማስ ዞሮ ለእራስ

Nebyu Tefery-Mekonnen/Flösheim

ሌላውን ለማጥመድ ጉድባ የማሰ ሰው
በቆፈረው ጉድጓድ እራሱ ገቢ ነው
"ሰውን ለመቅበር ጉድጓድ ስትምስ
አታዝልቀው
ድንገት ተገባህ መውጫው አሳር ነው"
"ዓሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል
የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል"
ሌላውን ለማጥቃት ህግ ስታረቅ
ለእኔስ ቢሆን ብለህ ተጠንቀቅ።
ድንጋይ በድንጋይ ላይ ግንባታ የካብከው
በቀላሉ ሲወድም የቅፅበት ክስተት ነው።
ከአባይ የከፋ አጥፊው ወያኔ ነው
አሁን ሞክሼዎቹን ያጣላቸው ማን ነው?
አባይ መቼ ጎዳን ዝንተዓለሙን ሲፈስ
እኛ የተጠቃነው በወያኔ መንታ ምላስ።
ሃያ ሁለት ወንዞች በሜዳ ሲፈሱ
ስልጣን ለማቆየት እያተራመሱ
ከአባይ ሽለቆ እንገድብ ተነሱ።
ጉዳዩ እንደዚህ ነው ወያኔ እወቀው
አሁን የዘራኸውን ማጨድህ አይቀሬ ነው።
አበው ሲተርቱ ያኔ እንደሰማነው
ጅብ ይገባል አሉ ውሻ በቀደደው
የጎጠኛው ቡቺ ታሪኩ እንደዚህ ነው።

## ጎጠኛው ቡችላ




ውሻዬ ሞቶብኝ ለንብረቴ ሳስብ
ወዶ ገብ ቡችላ መጣ ከቤቴ ገብ
ይሄው ቡችላዬ በህፃንነቱ
መጮህ ሲያዘወትር እንደ እናት አባቱ
እኛስ መስሎን ነበር የሚከበር ቤቱ።
በሽታ ኮሽታ ሁሌ ሲደነፋ
ለቀንለት ሄድን  ግቢውን በተስፋ።
እቤት ስንመለስ ከየጉዳያችን
ለካስ ይዘረፋል ሁሌ ንብረታችን
እኛልብብለንሳንመለከተው
ጥቃቅኑ አልቆ ግዙፉን አጣነው።
በየጉሮኖው ዞረን ጀመርን ቆጠራ
አንድ ሁለት እያልን ሁሉንም በተራ።
እንስሶቹ ጎድለው ባዶ ነው ጉሮኖው
በችለማው ተገን ጅብ ሌባ አግዟቸው።
ጀሮአችን ከውጭ እኛ ከውስጥ ሆነን
በመጮህ በማልቀስ ብሎም በማላዘን
ለካ እየጠራ ነው ጅብና ሌቦችን።
ድምፁን ከፍ አድርጎ ወደላይ ሲያላዝን
መጣራቱ ነበር ከውጭ ሌቦችን
በጨኸቱ መሃል ቁጣውን ታሰማ
ለሌባ ሚስጥር ነው እኛ እንደማንሰማ
የግቢውን አጥር ዙሪያውን በመቅደድ
ለውጭው አራዊት ከፈተለት መንገድ
በዚህ በውሻችን እምነት ስለጠፋ
ነቅተን ስንጠብቅ እንቅልፋችን ጠፋ
በቤቱ ጭላንጭል ግቢውን ስንቃኘው
ውሻችን ከጅብ ጋር ሲላፋ አየነው።
ለካስ ይሄ ውሻ ገቡ ቡችላችን
ጮሆ በመናገር ያውቃል ሚስጥሮችን
በሁኔታው አዝና ድመት ብትጠይቀው
ጎጠኛ ነኝ አለ ወያኔ የላከው።

# TPLF atrocities on Ethiopian peoples

**Nahom Woldeyohannes/ Kirchheim**

The TPLF regime has now been in power for over 21 years, by the standards of democratic government anywhere in the world as opposed to the standards of African dictatorship. This is a very long time.

The extreme narrowness of the TPLF regime domestic base, The TPLF has never been able to rid itself of the sense that this is essentially a Tigray government through it has selected the so called ministers from a wide range of nationalities. The core of the regime has always lain in the TPLF that created it. Tigray with some 6% of the population ,provides much to narrow a base from which to governEthiopia, and once Ethiopians gained the chance to choose their own government, it is only to be expected that they should vote for parties that more evidently their own communities.

The TPLF at least outside tigray has never been able, or indeed has never been allowed to develop into an effective political organization whose regional leadership could exercise any autonomus authority, or represent the communities that they governed. For several years it has been deeply alienated from the regime and most Ethiopian towns remains stagnant backwaters, and government policy has ignored them. Most rural areas has been passive towards the government at best, resentful at worst.

The government attitude towards dissent has often been brutal and alienating except where the need to placate donor communities has induced restraints.

To sum up, the TPLF dictatorial regime suppression is still under way and the concern both of Ethiopians and of the international community should to do whatever they can to collapse this brutal regime.

# We must Struggle!

**Zenebech Mamo/Fulda**

The dictator regime woyane dominion expressed him by corruption and racism. We can`t separate woyane from racism as well as corruption. In Ethiopia, until woyane is on power, corruption can not be stopped.

Our country Ethiopia is in dire straits. The country lies in between remaining a united and disintegration. Additionally, we Ethiopians are continuing to suffer under operation.

When, the then Colonialized African countries grown up democratically, we are going back. It is ironic that, we were at a frontline of all Africans but today we are Africa`s tail. This is a national shame. Extra judicial killing, harassment, and displacement are a day today activities of the TPLF regime in Ethiopia.

Because of TPLF`s policies and propaganda, we suffer a lot. We tend to look through ethnic lines only. We fought each other several times and thousands are gone forever.and many are still languish in such earthly hell prisons. And also many have left their homeland to save their lifes.

Dear Ethiopian people do not be afraid! Don`t be intimidiated by the threats of tyrants. Avoid fear from your heart. We must struggle to build a better country.

Therefore, inorder to root out this problem, we should have to aside with Ethiopian people patriotic front guard for better Ethiopia.Unity is power!

# Wir wünschen gleichheit und freiheit

**Elsa Hagos/Lahntal**

Es soll eine Gleichheit geben,in der auch Freiheit herrscht.Für Äthiopischer Volk ist es heute unser starker Wünsch eine gleiche und freiheit, in de res keine nationals und religiöse differenzirung gibt. Der Wille unseres landes Äthiopen ist leider nicht in erfülung gegangen, da die EPRDF(Die Regirung) eine große, üble roll spielt hass und differenzierung zwischen Gläubigen verschiedenen Religionen stiftet.

EPRDF regiert unser land mit macht und Gewalt, das unser volk demokrate sehr vermisst und darunter leidet. Außerdem gibt EPRDF nur den eigenen partei Freiheit und versucht allen anderen parteien und bewegungen zu unterdrücken und erlöschen.

Das Äthiopische Volk lebt im moment im eigenen land als fremed, viele leiden im gefängnis.in dem land wo unsere väter früher in Frieden und gegenseitigem Respekt lebten, ist heute leider.

Danke EPRDF, Muslimen und christen zu feinde geworden. Lass uns bitte an den tapferen land denken, die für unsere Freiheit gekämpft haben, und heute leider im Gefängnis in hand der EPRDF leiden. So wie Sie sich für uns geopfert haben, müssen wir auch für Ihre Freiheit alles möglich tun.

# We are Responsible!

**Abraham Desta, Gney/Fulda**

The evil regime of EPRDF is attacking the young generations by making them turn their focus not on the ongoing political situation as an active citizen but folding its hands and watch them being conquered by western technologies and alien culture.

They are not interested anymore to take part in the current political decisions, but instead they are never idle to discuss a week-old match result in the English Premier League. The young generation has left the responsibility to old opposition leaders, to deal with the country's issue.

They retreat from the fact. What interest them are frivolous non-political matters. Now Ethiopia is gradually heading to disintegration; and unambiguously reaching to the dead end.

As an active young citizen I suggest to my fellow young citizens in and out of Ethiopia to be responsible and focus on shaping our country's future.




# የአድራሻ ለውጥ




ጥላ መጽሔት የአድራሻ ለውጥ አድርጋለች። ለውጡ ግን የጎዳናው ስምና የቤት ቁጥሩ ብቻ ነው።ስለዚህ ከሚቀጥለው እትም ጀምሮ አስተያየቶቻችሁንና መልዕክቶቻችሁን በሚከተለው አድራሻ መላክ ትችላላችሁ።

**Mesfin Abraha**
**An der obergeis 1**
**36251 Bad Hersfeld**

ሰሞኑን በሩሲያ መዲና ሞስኮ መካሄድ በጀመረው የአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ ውድድር ላይ ለሚሳተፉት አትሌቶቻችን መልካም እድል እንመኛለን!












# A corruption led regime

**Sisay Getachew/Vlotho**

No doubt that corruption is becoming a bone in the neck for Ethiopia and Ethiopian. Corruption from "Kebele" guard through the highest office in the Country is simply an open secret. The good old Ethiopian saying, quote, "Sishom yalbella sishar yiqochewal" (which litrally means the one who were not corrupted when he was official, will gonna regret latter) is probably a prophesis of the past for its present-day realization.

Take the wife of the ex prime minister Mrs.Azeb Mesfin. Everybody knows that she is corrupted. She accumulated quite reasonable number of housing under the cover name of her families who lives in different parts of the country and abroad. Even the so called Ethics & Anti-Corruption Commission (which I usually like to refer to as "Anti-Ethics & Art-of-Corruption Commission") was tipped of about this at least five years ago. But the lady (Ethiopian usually refer her as a mother of corruption) is an obedient servant of the person who occupied the highest office in the Country until last August; ask the top management of private banks and they will tell you how the lady is a conveyor belt of foreign currency transportation out of the country even when the country has got short of money to import basic medication the last 4 years. She used to take out hundreds and thousands of dollars, if not in millions, and you bet it, that is not going to be deposited in her own foreign account, if she had one at all. We have seen a 5 billion dollar deposit check with the name of her daughter Semhal Meles from America last month. You can see it here now.






**Demonstaration against inhuman regimes around the world, Munich– Germany!**
**29-06-2013**







**Ethiopian Ageazi Soldiers were brutally beaten the people who were protesting the government interference in religious issues in Kofele, Oromiya region**

**August 3/2013.**






# ጥላ መጽሔት ስምንተኛ እትም

**ጥላ መጽሔት 2ኛ ዓመት ስምንተኛ እትሟን ይዛ November 30/2013 ለንባብ ትበቃለች። ስለዚህ አዲስና ነባር ደንበኞቻችን በአዲሱ አድራሻችን ታገኙናላችሁ። በመጽሔታችን ላይ ያላችሁን አስተያየትና መልዕክቶች ሁሉ እስከ November 25/2013 ድረስ ልታደርሱን ትችላላችሁ።**

**ለበለጠ መረጃ የስልክ መስመራችንን መጠቀም ይቻላል።**

**WIR SIND IMMER FÜR SIE DA!**

**አዲሱ አድራሻችን**
**Mesfin Abraha**
**An der Obergeis 1**
**36251 Bad Hersfeld**
**E-Mail: tilamagazine@yahoo.de**
**Web-Site: tilamagazine.yolasite.com**
**Tel.No. 0152- 22195567**
**0176- 68830082, 0176-71668780**

**TILA MAGAZIN IST EURE MAGAZIN!**